# የአላህ ስሞችና ባሕሪያት

በ አቡ ሃይደር

## ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን፡፡(አል-ፋቲሃ 2) የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡

" اللَّهُ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى " سورة طه ٨

" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8

አምላካችን አላህ እሱ የሚጠራበትና የሚመለክበት የኾኑ ብዙ መልካም ስሞች አሉት፡፡ የእነዚህ ስሞች መብዛት ደግሞ የሚያመላክተው፡- በባሕሪያቱ እንከን አልባ የሆነ፣ችሎታው ፍጹም የተሟላ፣ ከፍጡራኑ ጋር የማይመሳሰል….. መሆኑን ነው፡፡ጌታችን አላህ በስሞቹ የሚጠራ፣በባሕሪያቱ የሚገለጽ፣በስራዎቹ የሚታወቅ አምላክ ነው፡፡ስሞቹም የሱን ማንነት፡ ባሕሪያቱንና ስራዎቹን ገላጭ ናቸው፡፡ እሱ እራሱን የሰየመባቸው ብዙ መለኮታዊ ስሞች አሉት፡፡

" وَلِلَّهِ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى فَادْعُوهُ بِهَا وَذَرُوا الَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِي أَسْمَائِهِ سَيُجْزَوْنَ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ " سورة الأعراف ١٨٠

" ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትጸልዩ) በርሷም ጥሩት እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተውዋቸው፤ ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይመነዳሉ።" ሱረቱል አዕራፍ 180

" قُلِ ادْعُوا اللَّهَ أَوِ ادْعُوا الرَّحْمَنَ أَيًّا مَا تَدْعُوا فَلَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى وَلَا تَجْهَرْ بِصَلَاتِكَ وَلَا تُخَافِتْ بِهَا وَابْتَغِ بَيْنَ ذَلِكَ سَبِيلًا " سورة الإسراء ١١٠

" አላህን ጥሩ፤ ወይም አልረሕማንን ጥሩ፤(ከሁለቱ) ማንኛውንም ብትጠሩ፣ (መልካም ነው)፤ ለርሱ መልካም ስሞች አሉትና በላቸው፤ በስግደትህም (ስታነብ)

አትጩህ፤ በርሷም ድምጽህን ዝቅ አታድርግ፤ በዚህም መካከል መንገድን ፈልግ።"
ሱረቱል ኢስራእ 110
" اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ " سورة طه ٨
" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8
" هُوَ اللَّهُ الْخَالِقُ الْبَارِئُ الْمُصَوِّرُ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ يُسَبِّحُ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة الحشر ٢٤
" እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው ቅርጽን አሳማሪው ነው፤ ለርሱ መልካሞች ስሞች አሉት፤ በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለርሱ ያሞግሳል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።" ሱረቱል ሐሽር 24
ከነዚህ አራት አንቀጾች የምንረዳው:- አላህ ብዙ መለኮታዊ ስሞች እንዳሉትና እነዚህም መለኮታዊ ስሞች " አል-ሑስና " (እጅግ ያማሩ) መሆናቸውን ነው፡፡ በነቢያችን (ዐለይሂ-ሶላቱ ወስ-ሰላም) ሃዲስ ውስጥም ጌታችን መለኮታዊ የሆኑ ስሞች እንዳሉት ተነግሮናል፡፡
عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ: أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ لِلَّهِ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ اسْمًا مِائَةً إِلَّا وَاحِدًا، مَنْ أَحْصَاهَا دَخَلَ الجَنَّةَ» رواه البخاري
عَنْ أَبِى هُرَيْرَةَ عَنِ النَّبِىِّ -صلى الله عليه وسلم- قَالَ « لِلَّهِ تِسْعَةٌ وَتِسْعُونَ اسْمًا مَنْ حَفِظَهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ وَإِنَّ اللَّهَ وِتْرٌ يُحِبُّ الْوِتْرَ » رواه مسلم
ከአቢ ሁረይራህ በተላለፈው ሃዲስ የአላህ ነቢይ እንዲህ አሉ:- " አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፡፡ እነዚህን ስሞች የሀፈዘ (በቃሉ ያጠና) ጀነት ገባ፡፡ አላህ ዊትር(አንድ) ነውና ዊትር ነገርንም ይወዳል " ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ በዚህ ሃዲስ መሰረት ጌታችን ዘጠና ዘጠኝ መለኮታዊ ስሞች እንዳሉት መረዳት እንችላለን፡፡ ያ ማለት ደግሞ ከዛ በላይ ሌሎች ስሞች የሉትም ማለት አይደለም፡፡ የተነገረንን በደንብ እናስተውል፡፡ ሃዲሱ የሚለው " አላህ 99 ስሞች አሉት " ነው እንጂ " የአላህ ስሞች 99 ናቸው " አይደለም፡፡ ተግባባን ወንድሞችና እህቶች? ወይስ በሁለቱ መሐል ያለውን ልዩነት ላስረዳቹ? መርሐባ፡፡ " አላህ 99 ስሞች አሉት " ማለት ማንም ሰው መረዳት እንደሚችለው እሱ ጌታችን አላህ 99 ስሞች

እንዳሉት ነው:: ነገር ግን ከዛ በላይ ሌሎች ስሞች የሉትም የሚለውን ከዚህ ቃል መረዳት አይቻልም:: በተቃራኒው ደግሞ:- " የአላህ ስሞች 99 ናቸው " ማለት ደግሞ የስሞቹን ብዛት በ 99 ገድበን እነዚህ ስሞች ብቻ እንዳሉት ነው የምንረዳው:: አሁንም ግልጽ ካልሆነላቹ ሌላ ምሳሌ ልስጣችሁ:: " እኔ መቶ ብር አለኝ " ብላችሁ እናንተ የምትረዱት በኪሴ ውስጥ መቶ ብር እንደያዝኩ እንጂ ከዛ በላይ እንዳልያዝኩ አይደለም:: ነገር ግን እኔ መቶ ብር አለኝ ከማለት ይልቅ " እኔ ያለኝ መቶ ብር ነው " ብላችሁ ደግሞ ከዛ በላይ ሌላ ብር እንደሌለኝ ትረዳላችሁ ማለት ነው::አረብኛውም ላይ የተቀመጠው አገላለጽ لِلَّهِ تِسْعَةٌ وَتِسْعُونَ اسْمًا የሚል እንጂ إن أسماء الله تسعة وتسعون የሚል አይደለም:: የሃዲሱም መልእክት በቦታው ላይ ለነበሩ ሰዎች አላህ ዘጠና ዘጠኝ መለኮታዊ ስሞች እንዳሉትና በነዚህም ስሞች አላህን እንዲለምኑና ወደ አላህ እንዲቃረቡባቸው ለማስተማር እንጂ የአላህን ስሞች በቁጥር ለመገደብ አይደለም:: ይበልጥ ይህንን ሃሳብ የሚያጠናክረው ሌላ ነቢያዊ ሃዲስ ደግሞ መኖሩ ነው::

عَنْ عَبْدِ اللهِ ابن مسعود رضي الله عنه، قَالَ : قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ : " مَا قَالَ عَبْدٌ قَطُّ إِذَا أَصَابَهُ هَمٌّ وَحَزَنٌ : اللَّهُمَّ إِنِّي عَبْدُكَ ، وَابْنُ عَبْدِكَ ، ابْنُ أَمَتِكَ ، نَاصِيَتِي بِيَدِكَ ، مَاضٍ فِيَّ حُكْمُكَ ، عَدْلٌ فِيَّ قَضَاؤُكَ ، أَسْأَلُكَ بِكُلِّ اسْمٍ هُوَ لَكَ ، سَمَّيْتَ بِهِ نَفْسَكَ ، أَوْ أَنْزَلْتَهُ فِي كِتَابِكَ ، أَوْ عَلَّمْتَهُ أَحَدًا مِنْ خَلْقِكَ ، أَوِ اسْتَأْثَرْتَ بِهِ فِي عِلْمِ الْغَيْبِ عِنْدَكَ ،.... إِلاَّ أَذْهَبَ اللَّهُ عَزَّ وَجَلَّ هَمَّهُ ، وَأَبْدَلَهُ مَكَانَ حُزْنِهِ فَرَحًا ، قَالُوا : يَا رَسُولَ اللهِ يَنْبَغِي لَنَا أَنْ نَتَعَلَّمَ هَؤُلاَءِ الْكَلِمَاتِ ؟ قَالَ : أَجَلْ ، يَنْبَغِي لِمَنْ سَمِعَهُنَّ أَنْ يَتَعَلَّمَهُنَّ. " رواه أحمد ٥/٢٦٧

ከዐብደላህ ኢብን መስዑድ በተላለፈው ሃዲስ የአላህ መልክተኛ እንዲህ አሉ:- " አንድ የአላህ ባሪያ ጭንቀትና ሃዘን ሲገጥመው :- አላህ ሆይ! እኔ ባሪያህ፣የባሪያህ ልጅ ነኝ፡ እኔነቴም ባንተ ቁጥጥር ስር ነው፡ ውሳኔህ በኔ ላይ ተፈጻሚ ነው፡ ፍርድህም ፍትሀዊ ነው፡ እኔም ያንተ በሆኑት ስሞችህ ኹሉ፡ ራስህን በሰየምክበት፡ በመጽሐፍህም ውስጥ በጠቀስከው፡ ከፍጡሮችህም ለማንኛውም ባሳወቅከው፡ አንተ ዘንድም ብቻህን ባወቅከው ስሞችህ እለምንሀለሁ .....አይልም አላህ ጭንቀቱንና ሃዘኑን ቢያስወግድለት፡ በምትኩም ደስታን ቢለግሰው እንጂ " ኢማሙ

አህመድ የዘገቡት፡፡
በዚህ ሃዲስ ውስጥ أَوِ اسْتَأْثَرْتَ بِهِ فِي عِلْمِ الْغَيْبِ عِنْدَكَ "አንተ ዘንድም ብቻህን ባወቅከው ስሞችህ" የሚለው የሚያመላክተን ጌታችን ራሱ ብቻ የሚያውቀው ከፍጡራን የተሰወረ መለኮታዊ ስሞች እንዳሉት ነው፡፡
ለምን አስፈለገ?
የአላህን ስሞችና ባሕሪያትን ስናጠና አላማ ሊኖረን ይገባል፡፡ ከፊት ለፊታችን ጥቅምን አስቀምጠን መሆን አለበት፡፡የአላህ ስሞችንና ባሕሪያትን ስንማር ብዙ ጥቅሞችን እናገኛለን፡፡ ከነዚህም መሐከል፡-

1. ጌታችንን ማወቅ

ከጌታ አላህ ስሞች እና ባሕሪያት ጋር በተዋውቅን ቁጥር ስለ አላህ ያለንም እውቀት በዛው መልኩ እያደገ ይመጣል፡፡ ምክንያቱም አላህ ባወረደው ቅዱስ ቁርኣኑ ላይ እራሱን ያስተዋወቀን፡ በስሞቹ፣ በባሕሪያቱና በስራዎቹ አማካይነት ነው፡፡ እነዚህን ስሞችና ባሕሪያትን ማወቅ ደግሞ ለአላህ ያለን ክብር ከፍ እንዲልና እንድንፈራው እንድናከብረውም ይረዳናል፡፡

2. ወደሱ መቃረብ

ሌላው ጥቅም ደግሞ፡- አላህን ለመለመንና በስሞቹም ወደሱ ለመቃረብ ይረዳናል፡፡ ተከታዩ የቁርኣን አንቀጽ ይህንን ያስረዳል፡፡
" وَلِلَّهِ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى فَادْعُوهُ بِهَا.... " سورة الأعراف ١٨٠
" ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትጸልዩ) በርሷም ጥሩት ...." ሱረቱል አዕራፍ 180

3. ጀነት መግባት

የመጨረሻውና ትልቁ ግብም ይኸው ነው፡፡ የአላህን ስሞች (ዘጠና ዘጠኙን) የሐፈዘ ጀነት ይገባል፡፡
عَنْ أَبِى هُرَيْرَةَ عَنِ النَّبِىِّ -صلى الله عليه وسلم- قَالَ « لِلَّهِ تِسْعَةٌ وَتِسْعُونَ اسْمًا مَنْ حَفِظَهَا دَخَلَ الْجَنَّةَ وَإِنَّ اللَّهَ وِتْرٌ يُحِبُّ الْوِتْرَ » رواه مسلم
ከአቢ ሁረይራህ በተላለፈው ሃዲስ የአላህ ነቢይ እንዲህ አሉ፡- " አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፡፡ እነዚህን ስሞች የሀፈዘ (በቃሉ ያጠና) ጀነት ገባ፡፡ አላህ ዊትር(አንድ) ነውና ዊትር ነገርንም ይወዳል " ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

እዚህ ላይ " مَنْ حَفِظَهَا ( የሀፈዘ"በቃሉ ያጠና" ) የሚለው ላይ የኢስላም ሊቃውንት (ዑለማእ) የሰጡትን ማብራሪያ መመልከት ይኖርብናል፡፡

قال ابن القيم: " مراتب إحصاء أسمائه التي من أحصاها دخل الجنة وهذا هو قطب السعادة ومدار النجاة والفلاح:

- المرتبة الأولى إحصاء ألفاظها وعددها.
- المرتبة الثانية فهم معانيها ومدلولها، والإحاطة بجميع معانيها.
- المرتبة الثالثة دعاؤه بها كما قال تعالى" وَلِلَّهِ الأَسْمَاءُ الْحُسْنَى فَادْعُوهُ بِهَا "الأعراف:١٨٠، وهو مرتبتان: إحداهما: دعاء ثناء وعبادة والثاني: دعاء طلب ومسألة، فلا يثنى عليه إلا بأسمائه الحسنى وصفاته العلى . " بدائع الفوائد ١٧١ باختصار

ኢማም ኢብኑል-ቀይም 691-751 ሒጅሪያ (ረሒመሁላህ) ሲያብራሩት፡-
የአላህን ስሞች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የሐፈዘ ጀነት ይገባል የሚለው የደስታ ሁሉ ቁንጮ እና የመዳን ዕምብርት ነው፡፡

ሀ. ስሞቹን ቃላቱን ከነ-ብዛታቸው መሐፈዝ (በቃል መያዝ)

ለ. የእነዚህን ስሞች ትርጓሜና መልክታቸውን በአግባቡ መረዳት

ሐ. በነዚህ ስሞች አላህን መለመንና እሱን ብቻ መገዛት፡፡ አላህ ራሱ እንደተናገረው፡- " ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትጸልዩ) በርሷም ጥሩት ….'' ሱረቱል አዕራፍ 180 እሱን ስንጠራውም፡-

1. የምስጋናና የውዳሴ ጥርሪዎችን በመጠቀም
2. የልመናና የአምልኮ ጥርሪዎችን በመጠቀም መሆን አለበት " በዳኢዑል-ፈዋኢድ ገጽ 171 በአጭሩ፡፡

የምንከተለው መርሆ

የአላህን ስሞችና ባህሪያትን አምነን የምንቀበለው ከዚህ በታች በተቀመጡት መስፈርቶች ሊሆን ይገባል፡፡

1. (( إثباتُ ما أثبته الله لنفسه في كتابه ، أو أثبته له رسوله صلى الله عليه وسلم ؛ من غير تحريف ولا تعطيل ، ومن غير تكييف ولا تمثيل)).

1. አላህ ለራሱ በቁርኣኑ ላይ ያጸደቀውን ወይም መልከተኛው በሃዲሳቸው ላይ

ያጸደቁትን ስም ቃላቱን ሳንቀይር፣ትርጉም ሳናሳጣው፣ እንዲሕ ይመስላል ሳንልና ከፍጡሩም ጋር ሳናመሳስለው ማጽደቅ፡፡
አላህ ስለ-ራሱ ከማንም በላይ ዐዋቂ ነው፡፡ መልክተኛው ደግሞ ከሁሉም በላይ ስል-ጌታቸው የበለጠ ዐዋቂ ናቸው፡፡ የኛ ድርሻ በቁርአንም ሆነ በሶሒሕ ሃዲስ የተነገረንን የአላህን ስሞችና ባሕሪያት እንዳመጣጡ መቀበልና ማጽደቅ ብቻ ነው፡፡
2. (( نفـيُ ما نفاه الله عن نفسه في كتابه ، أو نفاه عنه رسوله صلى الله عليه وسلم ، مع اعتقاد ثبوت كمال ضده لله تعالى)).
2. አላህ በቁርኣኑ ከራሱ ላይ ውድቅ ያደረገውን ወይም መልከተኛው በሃዲሳቸው ላይ ውድቅ ያደረጉትን ባህሪያት እኛም ውድቅ ማድረግ፡፡
ለጌታችን ተገቢ ያልሆኑ ባሕሪያትን በሙሉ በቅዱስ ቁርኣን ላይ እና በሃዲስ በተነገረን መሰረት እኛም ጌታችንን ከነዚህ ባህሪያት ማጽዳት ፡፡ ለምሳሌ፡- ዕንቅልፍ፣ልጅን መያዝ፣ጅህልና.....በተቃራኒው ሕያውነቱን፣አዋቂነቱን፣ከልጅ የጠራ መሆኑን ከማመን ጋር፡፡
3. (( صفات الله عَزَّ وجَلَّ توقيفية ؛ فلا يُثبت منها إلا ما أثبته الله لنفسه ، أو أثبته له رسوله صلى الله عليه وسلم ، ولا يُنفى عن الله عَزَّ وجَلَّ إلا ما نفاه عن نفسه ، أو نفاه عنه رسوله صلى الله عليه وسلم)).
3. የአላህን ስሞችና ባሕሪያት ማወቅ የሚቻለው በቁርአንና ሃዲስ ላይ በመጣው መልኩ ብቻ ነው፡፡ ከዛ ውጪ ከሌላ ምንጭ በመጠቀም ቁርኣን ውስጥና ሃዲስ ውስጥ የሌለን ስም እንደ ስሙ መያዝ፣ቁርኣንና ሃዲስ ያልተቃወሙትንም ስምና ባሕሪ እኛም ልንቃወም አይገባንም፡፡
አንድን ስም ወይም ባሕሪ የአላህ ነው ብሎ ለመቀበል የግድ ያ ስም በቁርኣን ወይም በሶሒሕ ሃዲስ ውስጥ መሰረት ሊኖረው ይገባል፡፡ በይሆናልና በግምት ወይም ከሌላ ምንጭ በመውሰድ አላህን መሰየም የተሳሳተ አካሄድ ነው፡፡ ውድቅም ስናደርግ እንደዛው በቁርኣንና ሃዲስ ላይ መገደብ ያስፈልገናል፡፡
4. ((صفات الله تعالى كلها صفات كمال ، لا نقص فيها بوجهٍ من الوجوه)).
4. የአላህ ስሞችና ባህሪያት በጠቅላላ ፍጹም ምሉእነትን የተላበሱ ናቸው፡፡ በምንም አይነት መልኩ ጉድለት አይጠጋቸውም፡፡
ኡለማዎች ብዙ መርሆችን አስቀምጠዋል፡፡ ለመግቢያ ያክል እነዚህ በቂ ናቸው፡፡

ከቀጣዩ ሳምንት ጀምሮ በአላህ ፈቃድ የምንመለከታቸው የአላህ ስሞች ተራ አቀማመጥ ከዚህ በታች ባለው ቪዲዮ መሰረት ስልሆነ እናንተም ያን በማየት እንድትዘጋጁ፡፡ ዘጠና ዘጠኙን ስሞች የሚጠቅሰው ሃዲስ ላይ የሃዲስ ሊቃውንት ሰነዱ ላይ ድክመት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ከውስጡም ስሞች ያልሆኑ ግን ባህሪ ውስጥ የሚካተቱም እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ሁሉንም በአላህ ፈቃድ በቦታው እናየዋለን ኢንሻአላህ፡፡

# የአላህ ስሞችና ባሕሪያት

በ አቡ ሃይደር

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡
ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን፡፡(አል-ፋቲሃ 2) የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡

" اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ " سورة طه ٨

" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8

## 1.አር-ራሕማን

### ሀ.ትርጓሜው

የዚህ መለኮታዊ ስም "አር-ራሕማን" ትርጉም፡- እጅግ በጣም ሩኅሩህ ማለት ነው፡፡ ርህራሄው ፍጥረቱን በመላ ያካለለ ለአማኙም ሆነ ለከሐዲው የተረፈ ነው፡፡ "አር-ራሕማን" የሚለው መለኮታዊ ሰም አላህ ብቻ ሚጠራበት ነው፡፡ ከሱ ውጪ ማንንም በዚህ ስም መጥራት አይፈቀድም፡፡ ከራህመቱ መገለጫዎችም፡- ባሬያዎቹን ፈጥሮ ለሲሳያቸውም ኃላፊነቱን ራሱ መውሰዱ፣የመኖሪያ ስፍራቸውን ዱንያን ያለ-ምንም ሽያጭና ኪራይ በነጻ መስጠቱ፣ነቢያትን ከመሐከላቸው መርጦ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን አውርዶ ወደ ቅን ጎዳና ማመላከቱና ማገዙ....ከፊሎቹ ናቸው፡፡የአላህ ራህመት ለባሪያዎቹ የተስፋ በርን የሚከፍት፤ ወደ መልካም ስራ የሚያነሳሳ እንዲሁም ፍርሐትና ተስፋ መቁረጥን የሚያርቅ ነው፡፡ ስለሆነም ነው ነቢያችን እንዲህ የተናገሩት፡- "ሙእሚን አላህ ለኃጢአተኞች ያዘጋጀውን ቅጣት ታላቅነት ቢረዳ ኖሮ ጀነቱን ተስፋ አያደርግም ነበር፤ ካፊር ደግሞ አላህ ለተመላሽ ባሪያዎቹ የደገሰውን የራህመቱን ታላቅነት ቢረዳ ከጀነቱ ተስፋ አይቆርጥም ነበር" (ሙስሊም የዘገበው)፡፡ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ ቂያማ እስከሚቆም ድረስ ጌታችን በምድራችን

ላይ ያወረደው ራህመት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ እንፈልጋለን? ከፈለግን ቀጣዩን ነቢያዊ ሃዲስ እንመልከት፡- -

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰማሁ አለ፡- "አላህ ራህመትን ከፈጠረው በኋላ ወደ መቶ ቦታ ከፈለው፡፡ ከዛም አንድ እጁን ወደ ምድር በማውረድ ዘጠና ዘጠኙን እሱ ዘንድ አኖረ፡፡ በዚህ አንድ ክፋይ ነው ፍጥረተት የሚተዛዘኑት፡ ፈረስ እነኳ ሳትቀር እግሯን ከልጇ ላይ እንዳትጎዳው በማሰብ የምታነሳው የዚሁ ራህመት ውጤት ነው" (ቡኻሪ የዘገበው)፡፡ በሌላ ዘገባ ላይ ደግሞ፡- የቂያም ዕለት መቶውንም የራህመት ክፍሎች ለአማኝ ባሪያዎቹ እንደሚለግሳቸው ተገልጻል፡፡ ጌታችን አላህ ከቁጣው ራህመቱ የቀደመ አምላክ ነው፡፡

ለ. አመጣጡ

"አር-ራሕማን" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ 57(ሃምሳ ሰባት) ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ለናሙና ያክል፡-

قَالَتْ إِنِّي أَعُوذُ بِالرَّحْمَنِ مِنْكَ إِنْ كُنْتَ تَقِيًّا » سورة مريم ١٨ «

"፡- እኔ ከአንተ በአልረሕማን እጠበቃለሁ፤ ጌታህን ፈሪ እንደ ኾንክ፣ (አትቅረበኝ) አለች።" ሱረቱ መርየም 18

إِذَا تُتْلَى عَلَيْهِمْ آيَاتُ الرَّحْمَنِ خَرُّوا سُجَّدًا وَبُكِيًّا » سورة مريم ٥٨ «

"የአልረሕማን አንቀጾች በነሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ፣ ሰጋጆችና አልቃሾች ኾነዉ ይወድቃሉ።" ሱረቱ መርየም 58

وَلَقَدْ قَالَ لَهُمْ هَارُونُ مِنْ قَبْلُ يَا قَوْمِ إِنَّمَا فُتِنْتُمْ بِهِ وَإِنَّ رَبَّكُمُ الرَّحْمَنُ فَاتَّبِعُونِي وَأَطِيعُوا أَمْرِي » سورة طه ٩٠ «

"ሃሩንም ከዚያ በፊት በእርግጥ አላቸው፡- ሕዝቦቼ ሆይ! (ይህ) በርሱ የተሞከራችሁበት ብቻ ነው ጌታችሁም አልረህማን ነው ተከተሉኝም፤ ትእዛዜንም ስሙ።" ሱረቱ ጣሀ 90

ይህ "አር-ራሕማን" የሚለው መለኮታዊ ስም ስምነትን ብቻ ሳይሆን ባሕሪንም ጭምር ያዘለ ነው፡፡ እሱም ጌታችን አላህ የራህመት ባሕሪ ባለቤት መሆኑን ያሳየናል፡፡ ለመለኮታዊ ክብሩ ተገቢ በሆነ መልኩ ከፍጡራን የርህራሄ ባሕሪ ጋር

ምንም ባልተመሳሰለ መልኩ አላህ የራህመት ባለቤት ነው፡፡
فَإِنْ كَذَّبُوكَ فَقُلْ رَبُّكُمْ ذُو رَحْمَةٍ وَاسِعَةٍ وَلَا يُرَدُّ بَأْسُهُ عَنِ الْقَوْمِ الْمُجْرِمِينَ » سورة «
العنعام ١٤٧
"ቢያስተባብሉህም፡- «ጌታችሁ የሰፊ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡ ብርቱ ቅጣቱም ከአመጸኞች ሕዝቦች ላይ አይመለስም» በላቸው፡፡" ሱረቱል አንዓም 147
ችሮታ ማለት እዝነት ቸርነት የሚለውን የሚገልጽ ነው፡፡ ከፍጡራን ጋር ምንም የሚያመሳስለው ነገር የለም፡- "ለአላህም አምሳያዎችን አታድርጉ፤ አላህ (መሳይ እንደሌለው) ያውቃል፤ እናንተ ግን አታውቁም" (ሱረቱ-ነሕል 74)፡፡ እንዲሁም፡- "(እርሱ) የሰማያትና የምድር፣ በሁለቱም መካካል ላለዉ ሁሉ ጌታ ነዉና ተገዛዉ፤ እርሱን በመግገዛትም ላይ ታገሥ፤ ለርሱ ሞክሼን ታዉቃለህን ?" (ሱረቱ መርየም 65)፡፡ እንዲሁም፡- "…የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው" (ሱረቱ-ሹራ 11)፡፡ እንዲሁም፡-"ለርሱም አንድም ብጤ የለውም" (ሱረቱል-ኢኽላስ 4) የሚሉትን ተመልከት፡፡
ሐ. የምንወስደው ትምሕርት
ከዚህ "አር-ራሕማን" ከሚለው መለኮታዊ ስሞች ብዙ ጠቀሚ ነገሮችን እንወስዳለን፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-
1. "አር-ራሕማን" የሚል ስም እንዳለው፡- ፈጣሪ አምላካችን አላህ እርሱ "አር-ራሕማን" መሆኑን እንረዳለን፡፡አምነንም እንቀበላለን፡፡
قُلْ هُوَ الرَّحْمَنُ آمَنَّا بِهِ وَعَلَيْهِ تَوَكَّلْنَا فَسَتَعْلَمُونَ مَنْ هُوَ فِي ضَلَالٍ مُبِينٍ » سورة «
الملك ٢٩
"እርሱ (እመኑበት የምላችሁ) አልረሕማን ነው፤ (እኛ) በርሱ አመንን፤ በርሱም ላይ ተጠጋን፤ ወደ ፊትም በግልጽ መሳሳት ውስጥ የሆነው እርሱ ማን እንደ ሆነ በእርግጥ ታውቃላችሁ በላቸው።" ሱረቱል ሙልክ 29
2. ይህ ስም የ ራህመት ባሕሪን እንዳቀፈ፡- ጌታችን በርህራሄና በቸርነቱ የሚታወቅ በዚህም ባህሪ የሚገለጽ እንደሆነ እንረዳለን፡፡
وَرَبُّكَ الْغَنِيُّ ذُو الرَّحْمَةِ إِنْ يَشَأْ يُذْهِبْكُمْ وَيَسْتَخْلِفْ مِنْ بَعْدِكُمْ مَا يَشَاءُ كَمَا أَنْشَأَكُمْ «
مِنْ ذُرِّيَّةِ قَوْمٍ آخَرِينَ » سورة الأنعام ١٣٣

"ጌታህም ተብቃቂ የእዝነት ባለቤት ነው፡፡ ቢሻ ያስወግዳችኋል፤ (ያጠፋችኋል)፡፡ ከሌሎች ሕዝቦችም ዘሮች እንዳስገኛችሁ ከበኋላችሁ የሚሻውን ይተካል፡፡" ሱረቱል አንዓም 133

3. ማመስገን እንዳለብን፡- "አር-ራሕማን" የሆነው አምላካችን አላህ ከራህመቱ ስፋት የተነሳ ቀኑን እንድንሰራበትና ሲሳያችንን እንድንፈልግበት ብርሐን፣ ሌሊቱን ደግሞ እንድናርፍበት ጨለማ አድርጎልናል፡፡ በዚህ ራህመቱም እንድናመሰግነው ይፈልጋል፡፡ አልሃምዱ ሊላሂ ረቢል ዓለሚን፡፡

« وَمِنْ رَحْمَتِهِ جَعَلَ لَكُمُ اللَّيْلَ وَالنَّهَارَ لِتَسْكُنُوا فِيهِ وَلِتَبْتَغُوا مِنْ فَضْلِهِ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ » سورة القصص ٧٣

"ከችሮታውም ለእናንተ ሌሊትንና ቀንን በውስጡ ልታርፉበት፣ ከትሩፋቱም ልትፈልጉበት፣ አመስገኞችም ልትኾኑ አደረገላችሁ፡፡" ሱረቱል ቀሰስ 73

4. በዚህ ስም እንድንለምነው፡- ጌታችን አላህን ስንለምነውና ስንማጸነው "ያ አላህ" እንደምንለው ሁሉ "ያ ራህማን" ብለንም መማጸንና መለመን እንችላለን፡፡

« قُلِ ادْعُوا اللَّهَ أَوِ ادْعُوا الرَّحْمَنَ أَيًّا مَا تَدْعُوا فَلَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى » سورة الإسراء ١١٠

"፡-አላህን ጥሩ፤ ወይም አልረሕማንን ጥሩ፤(ከሁለቱ) ማንኛውንም ብትጠሩ፣ (መልካም ነው)፤ ለርሱ መልካም ስሞች አሉትና በላቸው…" ሱረቱል ኢስራእ 110

5. ባርነትን ወደዚህ ስም ማስጠጋትን፡- "አር-ራሕማን" የጌታችን ስም እስከሆነ ድረስ እኛም ባርነታችንን ወደዚህ ስም በማስጠጋት "ዐብዱ-ራሕማን" "አመቱ-ራሕማን" ብለን መሰየም፣ ስም ማውጣት እንችላለን፡፡

« إِنْ كُلُّ مَنْ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ إِلَّا آتِي الرَّحْمَنِ عَبْدًا » سورة مريم ٩٣

"በሰማያትና በምድር ያለዉ ሁሉ (በትንሣኤ ቀን)፣ ለአልረሕማን ባሪያ ኾነዉ የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።" ሱረቱ መርየም 93

« وَعِبَادُ الرَّحْمَنِ الَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى الْأَرْضِ هَوْنًا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ الْجَاهِلُونَ قَالُوا سَلَامًا » سورة الفرقان ٦٣

"የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚኼዱት፣ ባለጌዎችም

(በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ፣ ሰላም የሚሉት ናቸው።" ሱረቱል ፉርቃን 63
ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-"አላህ ዘንድ ከተወደዱት ስሞቻችሁ ውስጥ "ዐብደላህ" እና "አብዱ-ራሕማን" ናቸው" (ሙስሊም 2132)
በዚህ ስም ከተጠሩት የዚህ ኡመት ግንባር ቀደም ተጠቃሹ ታላቁ ሶሐቢይ "ዐብዱ-ራህማን ኢብኑ ዐውፍ" ነው፡፡ በሒጅራ አቆጣጠር 32ኛው አመት ላይ የሞተ፤ ጀነት ከተበሰሩት አስሩ ሰሐባዎች አንዱ ነው ረዲየላሁ ዐንሁ፡፡
6. ይህን ባህሪ መላበስ እንዳለብን፡- "አር-ራሕማን" የሆነው አምላካችን አላህ በመለኮታዊ ባህሪው ለባሪያዎቹ ርኅሩህ እንደሆነው እኛም በፍጥረታዊና ደካማ ባህሪያችን ለመሰል ወንድሞቻችንና ለእንሰሳት ርኅሩህ መሆን እንዳለብን እንማራለን፡፡
ዐብደላህ ኢብኑ አምር (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-"አዛኞችን አር-ራሕማን ያዝንላቸዋል፡፡ የምድር ነዋሪዎች ሆይ! እዘኑ፤ ከሰማይ በላይ ያለው ያዝንላችኃልና" ( ቲርሚዚ 1924

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት
በ አቡ ሃይደር
ክፍል ሶስት
በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡
ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፉቲሃ 2) ፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡
" اللَّهُ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى " سورة طه ٨
" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8
ባለፈው ክፍል ሁለት ዓምዳችን ላይ በቁጥር 1 ስር የመጀመሪያውን መለኮታዊ ስም "አር-ራሕማን" የሚለውን በተወሰነ መልኩ ትርጓሜውን ቃኝተን ነበር፡፡ ዛሬ ቀጣይ ክፍሉ ይቀርባል ኢንሻአላህ፡፡

2. አር-ረሒም

ሀ.ትርጓሜው

የዚህ መለኮታዊ ስም "አር-ረሒም" ትርጉም፡- እጅግ በጣም አዛኝ ማለት ነው፡፡ እዝነቱ ምእመናን ባሮቹንና በተውበት የሚመለሱትን ያካለለ ስም ነው፡፡
"አር-ረሒም" የሚለው ስም "አር-ራሕማን" ከሚለው ስም ጋር ያለውን ልዩነት ሊቃውንት ካስቀመጡት ነጥቦች ውስጥ ሁለቱን እንመልከት፡-
- "አር-ራሕማን" የሚለው ስም የሚያመለክተው የጌታችንን የህልውናው (የዛቱ) መጠሪያ ስም ሲሆን "አር-ረሒም" ደግሞ በስራና በተግባር የሚገለጸውን የባሕሪ ስም አመልካች ነው፡፡
- "አር-ራሕማን" የሚለው ስም በዚህ አለም ላይ ለፍጡራኑ በጠቅላላ ለሙስሊሙም ለካፊሩም አዛኝነቱን የሚያመላክት ስም ነው፡፡ ጸሐይ ቢወጣ፣ ዝናብ ቢዘንብ፣ ምድር ብታበቅል የሚዳረሰው ለሁሉም ነውና፡፡ "አር-ረሒም" ግን ለአማኞች ብቻ የሚገለጽ የራህመት አይነት ነው፡፡ ለዚህም እንደማስረጃነት የሚቀርበው ተከታዩ አንቀጽ ነው፡-
« هُوَ الَّذِي يُصَلِّي عَلَيْكُمْ وَمَلَائِكَتُهُ لِيُخْرِجَكُمْ مِنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ وَكَانَ بِالْمُؤْمِنِينَ رَحِيمًا» سورة الأحزاب ٤٣
"እነሱ ያ በናንተ ላይ እዝነትን የሚያወርድ ነው፤ መላእክቶችም ፥ ( እንደዚሁ ምሕረትን የሚለምኑላችሁ ናቸው) ፣ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያመጣችሁ ዘንድ (ያዝንላችኋል)፤ ለአማኞችም በጣም አዛኝ ነው።" ሱረቱል አሕዛብ 43
« يَوْمَ لا يُغْنِي مَوْلًى عَن مَّوْلًى شَيْئاً وَلا هُمْ يُنصَرُونَ * إِلا مَن رَّحِمَ اللهُ إِنَّهُ هُوَ الْعَزِيزُ الرَّحِيمُ » سورة الدخان ٤٢-٤١
"ዘመድ ከዘመዱ ምንንም የማይጠቅምበት፣ እነሱም የማይረረዱበት ቀን ነው።አላህ ያዘነለት ብቻ ሲቀር፤ (እርሱስ ይረረዳል)፤ እርሱ አሸናፊው አዛኙ ነውና።" ሱረቱ-ዱኻን 41-42

ለ. አመጣጡ

"አር-ረሒም" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርአን ውስጥ 114 ጊዜ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-
" وَإِذْ قَالَ مُوسَى لِقَوْمِهِ يَا قَوْمِ إِنَّكُمْ ظَلَمْتُمْ أَنْفُسَكُمْ بِاتِّخَاذِكُمُ الْعِجْلَ فَتُوبُوا إِلَى بَارِئِكُمْ فَاقْتُلُوا أَنْفُسَكُمْ ذَلِكُمْ خَيْرٌ لَكُمْ عِنْدَ بَارِئِكُمْ فَتَابَ عَلَيْكُمْ إِنَّهُ هُوَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ " سورة البقرة ٥٤
"ሙሳም ለሕዝቦቹ፡- «ሕዝቦቼ ሆይ! እናንተ ወይፈንን (አምላክ አድርጋችሁ) በመያዛችሁ ነፍሶቻችሁን በደላችሁ፡፡ ወደ ፈጣሪያችሁም ተመለሱ፤ ነፍሶቻችሁንም ግደሉ*** ይሃችሁ በፈጣሪያችሁ ዘንድ ለናንተ በላጭ ነው» ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በእናንተም ላይ ጸጸትን

በመቀበል ተመለሰላችሁ፡፡ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡" ሱረቱል በቀራህ 54
" وَلِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ يَغْفِرُ لِمَنْ يَشَاءُ وَيُعَذِّبُ مَنْ يَشَاءُ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ " سورة آل عمران ١٢٩
"በሰማያት ያለዉ፣ በምድርም ያለዉ፣ ሁሉ፣ የአላህ ነዉ፤ ለሚሻዉ ሰዉ ይምራል፤ የሚሻዉንም ሰዉ ይቀጣል፤ አላህም ማሐሪ አዛኝ ነዉ።" ሱረቱ አለ ዒምራን 129
" فَمَنْ تَابَ مِنْ بَعْدِ ظُلْمِهِ وَأَصْلَحَ فَإِنَّ اللَّهَ يَتُوبُ عَلَيْهِ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ " سورة المائدة ٣٩
"ከመበደሉም በኋላ የተጸጸተና ሥራውን ያሳመረ አላህ ጸጸቱን ከርሱ ይቀበለዋል፤ አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።" ሱረቱል ማኢዳህ 39
ሐ. የምንማረው ትምሕርት
"አር-ረሒም" ከሚለው መለኮታዊ ስም ብዙ ትምሕርት እናገኛለን፡፡ ከነዚህም መካከል፡-
1. ጌታችን "አር-ረሒም" የሚል መለኮታዊ ስም እንዳለው እንረዳለን፡፡ አምነንም እንቀበላለን፡፡
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ عَالِمُ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ هُوَ الرَّحْمَنُ الرَّحِيمُ " سورة الحشر ٢٢
"እርሱ አላህ ነው፤ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የሆነው፤ እርሱ እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ ነው።" ሱረቱል ሐሽር 22
2. በዚህ ስም እንድንለምነው፡- ጌታችን አላህን ስንለምነውና ስንማጸነው "ያ አላህ" እንደምንለው ሁሉ "ያ ረሒም" ብለንም መማጸንና መለመን እንችላለን፡፡
" [قَالَ رَبِّ إِنِّي ظَلَمْتُ نَفْسِي فَاغْفِرْ لِي فَغَفَرَ لَهُ إِنَّهُ هُوَ الغَفُورُ الرَّحِيمُ " [القصص:١٦
"«ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ፡፡ ለእኔም ማር አለ፡፡» ለእርሱም ምሕረት አደረገለት እርሱ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡" ሱረቱል ቀሶስ 16
3. ባሕሪውን መላበስን፡- ጌታችን አላህ በባሕሪውም ሆነ በስሞቹ ከፍጡራን ጋር አይመሳሰልም(ሹራ 11)፡፡ ለፍጡር ባሪያው ግን ከማንነቱ ጋር ተስማሚ የሆነ ባህሪ ለግሶታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ እዝነት ነው፡፡ እርሱ ጌታችን "አር-ረሒም" ነውና ለባሪያውም እዝነትን ለገሰ፡፡ በተለይ ለነቢያችን የተለገሰው ባሕሪ ነው፡፡ ተከታዮቹ አንቀጾች ይህን ይገልጻሉ፡-
" لَقَدْ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مِنْ أَنْفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُمْ بِالْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَحِيمٌ " سورة التوبة ١٢٨
"ከነሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በርሱ ላይ ጥኑ የሆነ፣ በናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእምናን ርኅሩህ አዛኝ የሆነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ።" ሱረቱ-ተውባህ 128
" وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِلْعَالَمِينَ " سورة الأنبياء ١٠٧
" (ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።" ሱረቱል አንቢያእ 107
3. አል-መሊክ
ሀ. ትርጓሜው

የዚህ መለኮታዊ ስም "አል-መሊክ" ትርጉም፡- ንጉስ እና ባለቤት(ማሊክ) ማለት ነው፡፡ ፍጥረተ ዓለሙ በጠቅላላ የተገኘው በጌታችን አላህ ጥበብና ችሎታ በመሆኑ እሱ የዓለሙ ሁሉ ባለቤት ነው ማለት ነው፡፡ ፈጥሮና አስገኝቶም በተግባር ዓለሙን ሲመራና ሲያስተናብር ደግሞ "ንጉስ" ይሰኛል ማለት ነው፡፡
ጌታችን አላህ ብቻውን ንጉስ ነው፡፡ በንግስናው ተጋሪ የለውም፡፡
" الَّذِي لَهُ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَلَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُنْ لَهُ شَرِيكٌ فِي الْمُلْكِ وَخَلَقَ كُلَّ شَيْءٍ فَقَدَّرَهُ تَقْدِيرًا " سورة الفرقان ٢
" (እርሱ) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና የርሱ ብቻ የሆነ ልጅንም ያልያዘ፣ በንግሥናውም ተጋሪ የሌለው፣ ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና፣ በትክክልም ያዘጋጀው ነው።" ሱረቱል ፉርቃን 2
" وَقُلِ الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي لَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُنْ لَهُ شَرِيكٌ فِي الْمُلْكِ وَلَمْ يَكُنْ لَهُ وَلِيٌّ مِنَ الذُّلِّ وَكَبِّرْهُ تَكْبِيرًا " سورة الإسراء ١١١
"፡-ምስጋና ለአላህ ለዚያ ልጅን ላልያዘነው ለርሱም በንግሥናው ተጋሪ ለሌለው ለርሱም ከውርደት ረዳት ለሌለው ይግባው፣ በልም ማክበርን አክብረው።" ሱረቱል ኢስራእ 111
ለ. አመጣጡ
"አል-መሊክ" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርአን ውስጥ 5 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡
" فَتَعَالَى اللَّهُ الْمَلِكُ الْحَقُّ ... " سورة طه ١١٤
"እውነተኛው ንጉስ አላህም(ከሃዲዎች ከሚሉት)ላቀ …" ሱረቱ ጣሀ 114
" إِنَّ الْمُتَّقِينَ فِي جَنَّاتٍ وَنَهَرٍ * فِي مَقْعَدِ صِدْقٍ عِنْدَ مَلِيكٍ مُقْتَدِرٍ " سورة القمر ٥٤-٥٥
"አላህን ፈሪዎች በአትክልቶችና በወንዞች ዉስጥ ናቸው፤(እነሱም ውድቅ ቃልና መወንጀል በሌለበት) በውነት መቀመጫ ዉስጥ ቻይ እሆነው ንጉስ ዘንድ ናቸው" ሱረቱል ቀመር 54-55
" فَتَعَالَى اللَّهُ الْمَلِكُ الْحَقُّ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ رَبُّ الْعَرْشِ الْكَرِيمِ " سورة المؤمنون ١١٦
"የእውነቱም ንጉስ አላህ ከፍተኛነት ተገባው፡፡ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ የሚያምረው ዐርሽ ጌታ ነው፡፡" ሱረቱል ሙእሚኑን 116
ሐ. የምንወስደው ትምሕርት፡-
1. ጌታችን "አል መሊክ" የሚል መለኮታዊ ስም እንዳለው እንረዳለን፡፡ አምነንም እንቀበላለን፡፡
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣

"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" ሱረቱል ሐሽር 23
" يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ الْمَلِكِ الْقُدُّوسِ الْعَزِيزِ الْحَكِيمِ " سورة الجمعة ١
"በሰማያት ያለው በምድርም ያለው ሁሉ ለአላህ ንጉሥ፣ ቅዱስ፣ አሸናፊ፣ ጥበበኛ ለሆነው

ያሞግሳል።" ሱረቱል ጁሙዓህ 1
2. ንግስና የሱ ብቻ መሆኑን፡- -በዚህ በምድረ ዓለም ላይ የነገሰ ዓለሙን የሚገዛ ብቸኛ ንጉስ አላህ ብቻ ነው፡፡
"... يَخْلُقُكُمْ فِي بُطُونِ أُمَّهَاتِكُمْ خَلْقًا مِنْ بَعْدِ خَلْقٍ فِي ظُلُمَاتٍ ثَلَاثٍ ذَلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمْ لَهُ الْمُلْكُ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ فَأَنَّى تُصْرَفُونَ " سورة الزمر ٦
"...በእናቶቻችሁ ሆዶች ውስጥ፣ በሦስት ጨለማዎች ውስጥ፣ ከመፍጠር በኋላ፣ (ሙሉ) መፍጠርን ይፈጥራችኋል፤ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው። ሥልጣኑ የርሱ ብቻ ነው፤ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ።" ሱረቱ-ዙመር 6
" يُولِجُ اللَّيْلَ فِي النَّهَارِ وَيُولِجُ النَّهَارَ فِي اللَّيْلِ وَسَخَّرَ الشَّمْسَ وَالْقَمَرَ كُلٌّ يَجْرِي لِأَجَلٍ مُسَمًّى ذَلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمْ لَهُ الْمُلْكُ وَالَّذِينَ تَدْعُونَ مِنْ دُونِهِ مَا يَمْلِكُونَ مِنْ قِطْمِيرٍ " سورة فاطر ١٣
"ሌሊትን በቀን ውስጥ ያስገባል፤ ቀንንም በሌሊት ውስጥ ያስገባል፤ ፀሐይንና ጨረቃንም ገራ፤ ሁሉም እተወሰነ ጊዜ ድረስ ይሮጣሉ፤ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፤ ንግሥናው የርሱ ብቻ ነው፤ እነዚያም ከርሱ ሌላ የምትግገዟቸው የተምር ፍሬ ሺፋን እንኳ አይኖራቸውም።" ሱረቱ ፋጢር 13
" يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ " سورة التغابن ١
"በሰማያት ውስጥ ያለው በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ ለአላህ ያሞግሳል፤ ንግሥናው የርሱ ብቻ ነው፤ ምስጋናም ለርሱ ነው፤ እርሱም በነገሩ ቻይ ነው።" ሱረቱ-ተጋቡን 1
" تَبَارَكَ الَّذِي بِيَدِهِ الْمُلْكُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ " سورة الملك ١
"ያ ንግሥና በእጁ የሆነው አምላክ ችሮታው በዛ፤ እርሱም በነገሩ ሁሉ ቻይ ነው።" ሱረቱል ሙልክ 1
3. ንጉስን የሚሾም የሚሽር እሱ ብቻ መሆኑን፡-
" رَبِّ قَدْ آتَيْتَنِي مِنَ الْمُلْكِ وَعَلَّمْتَنِي مِنْ تَأْوِيلِ الْأَحَادِيثِ فَاطِرَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ أَنْتَ وَلِيِّي فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ تَوَفَّنِي مُسْلِمًا وَأَلْحِقْنِي بِالصَّالِحِينَ " سورة يوسف ١٠١
"ጌታዬ ሆይ! ከንግስና በእርግጥ ሰጠኸኝ፤ ከሕልሞችም ፍች አስተማርከኝ፤ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ፤ ሙስሊም ሆኜ ግደለኝ፤ በመልካሞቹም አስጠጋኝ፤ (አለ)።" ሱረቱ ዩሱፍ 101
" قُلِ اللَّهُمَّ مَالِكَ الْمُلْكِ تُؤْتِي الْمُلْكَ مَنْ تَشَاءُ وَتَنْزِعُ الْمُلْكَ مِمَّنْ تَشَاءُ وَتُعِزُّ مَنْ تَشَاءُ وَتُذِلُّ مَنْ تَشَاءُ بِيَدِكَ الْخَيْرُ إِنَّكَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ " سورة آل عمران ٢٦
" (ሙሐመድ ሆይ!) በል- የንግሥና ባለቤት የሆንክ አላህ ሆይ! ለምትሻዉ ሰዉ ንግሥናን ትሰጣለህ፤ ከምትሻዉም ሰዉ ንግስናን ትገፍፋለህ፤ የምትሻዉንም ሰዉ ታልቃለህ፤ የምትሻዉንም ሰዉ ታዋርዳለህ። መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና።" ሱረቱ አለ-ዒምራን 26
4. በመጨረሻው ዓለምም ብቸኛ ንጉስ እሱ ብቻ መሆኑን፡-
" مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ " سورة الفاتحة ٤

" የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው (ምስጋና ይገባው)" ሱረቱል ፋቲሐ 4
"... وَيَوْمَ يَقُولُ كُنْ فَيَكُونُ قَوْلُهُ الْحَقُّ وَلَهُ الْمُلْكُ يَوْمَ يُنْفَخُ فِي الصُّورِ عَالِمُ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ وَهُوَ الْحَكِيمُ الْخَبِيرُ " سورة الأنعام ٧٣
"...«ኹን» የሚልበትንና ወዲያውም የሚኾንበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ቃሉ እውነት ነው፡፡ በቀንዱም በሚነፋ ቀን ንግሥናው የርሱ ብቻ ነው፡፡ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ ነው፡፡ እርሱም ጥበበኛው ውስጥ ዐዋቂው ነው፡፡" ሱረቱል አንዓም 73
" الْمُلْكُ يَوْمَئِذٍ لِلَّهِ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فَالَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ فِي جَنَّاتِ النَّعِيمِ " سورة الحج ٥٦
"በዚያ ቀን፣ ንግሥናው የአላህ ብቻ ነው፣ በመካከላቸው ይፈርዳል፤ እነዚያም ያመኑት፣ መልካም ሥራዎችንም የሠሩት፣ በመደሰቻ ገነቶች ውስጥ ናቸው።" ሱረቱል ሐጅ 56
" الْمُلْكُ يَوْمَئِذٍ الْحَقُّ لِلرَّحْمَنِ وَكَانَ يَوْمًا عَلَى الْكَافِرِينَ عَسِيرًا " سورة الفرقان ٢٦
"እውነተኛው ንግሥና በዚያ ቀን ለአልረሕማን ብቻ ነው፤ በከሓዲዎችም ላይ አስቸጋሪ ቀን ነው። " ሱረቱል ፋርቃን 26
" يَوْمَ هُمْ بَارِزُونَ لَا يَخْفَى عَلَى اللَّهِ مِنْهُمْ شَيْءٌ لِمَنِ الْمُلْكُ الْيَوْمَ لِلَّهِ الْوَاحِدِ الْقَهَّارِ " سورة غافر ١٦
"እነርሱ ከመቃብር (በሚወጡበት) ቀን፣ በአላህ ላይ ከነሱ ምንም ነገር አይደበቅም፤ ንግሥናው ዛሬ ለማን ነው? (ይባላል)፤ ለአሸናፊው ለአንዱ አላህ ብቻ ነው (ይባላል)።" ሱረቱ ጋፊር 16
ይቀጥላል

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት

በ አቡ ሃይደር

ክፍል አራት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሃ 2) ፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56)

ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡
ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡
" اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ " سورة طه ٨
" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8
4. "አል-ቁዱስ"
ሀ. ትርጉሙ
የዚህ መለኮታዊ ስም "አል-ቁዱስ" ትርጉም፡- ከነውር የጸዳ የምሉዕ ባሕሪያት ባለቤት ማለት ነው፡፡
ለ. አመጣጡ
"አል-ቁዱስ" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡-
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣
"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" (ሱረቱል ሐሽር 23)፡፡
" يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ الْمَلِكِ الْقُدُّوسِ الْعَزِيزِ الْحَكِيمِ " سورة الجمعة ١
"በሰማያት ያለው በምድርም ያለው ሁሉ ለአላህ ንጉሥ ቅዱስ አሸናፊ ጥበበኛ ለሆነው ያሞግሳል።" (ሱረቱል ጁሙዓህ 1)፡፡
وعند مسلم من حديث عائشة رضي الله عنها أن رسول الله صلى الله عليه وسلم كان يقول في ركوعه وسجوده : ( سُبُّوحٌ قُدُّوسٌ رَبُّ المَلاَئِكَةِ وَالرُّوحِ )
አዒሻ (ረዲየላሁ ዐንሃ) እንዲህ አለች፡- የአላህ መልክተኛ በሩኩዕ ላይ ሁነው፡- "ሱቡሕ፣ቁዱስ፣ረቡል መላኢከቲ ወር-ሩሕ" ይሉ ነበር፡፡ (ሙስሊም)፡፡
ሐ. የምንወስደው ትምሕርት

-ጌታችን ከጉድለት የጠራ ንጹህ መሆኑን፡-
" وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي جَاعِلٌ فِي الْأَرْضِ خَلِيفَةً قَالُوا أَتَجْعَلُ فِيهَا مَنْ يُفْسِدُ فِيهَا وَيَسْفِكُ الدِّمَاءَ وَنَحْنُ نُسَبِّحُ بِحَمْدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَ قَالَ إِنِّي أَعْلَمُ مَا لَا تَعْلَمُونَ " سورة البقرة ٣٠
"(ሙሐመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፡- «እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤» ባለ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ፤ እነርሱም) «እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን?» አሉ፡፡ (አላህ) «እኔ የማታውቁትን ነገር አውቃለሁ» አላቸው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 30)፡፡
5. "አስ-ሰላም"
ሀ. ትርጉሙ፡-
"አስ-ሰላም" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- የሰላም ባለቤት፤ ነውር አልባ የሚል ነው፡፡
ለ. አመጣጡ፡-
"አስ-ሰላም" የሚለው ስም በቅዱስ ቁርአን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፡-
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣
"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" (ሱረቱል ሐሽር 23)፡፡
ሐ. የምንማረው
1. እርሱ የሰላም ባለቤት መሆኑን፡- ጌታችን "አስ-ሰላም" በመሆኑ ሰላም የሚገኘው ከሱ ዘንድ ብቻ ነው፡፡
" تَحِيَّتُهُمْ يَوْمَ يَلْقَوْنَهُ سَلَامٌ وَأَعَدَّ لَهُمْ أَجْرًا كَرِيمًا " سورة الأحزاب ٤٤
"በሚገናኙት ቀን መከባበሪያቸው ሰላም በመባባል ነው፤ ለነርሱም የከበረን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል።" (ሱረቱል አሕዛብ 44)፡፡
" سَلَامٌ قَوْلًا مِنْ رَبٍّ رَحِيمٍ " سورة يس ٥٨

"(ለነሱም) አዛኝ ከሆነው ጌታ ቃል በቃል ሰላምታ አላቸው።" (ሱረቱ ያሲን 58)፡፡
ሶላታችንን ሰግደን ስናጠናቅቅ ከሶስት ጊዜ "አስተግፊሩላህ" በኋላ የምንለው ዚክርም ይህን ያመላክታል፡-
عَنْ ثَوْبَانَ، قَالَ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، إِذَا انْصَرَفَ مِنْ صَلَاتِهِ اسْتَغْفَرَ ثَلَاثًا وَقَالَ: «اللهُمَّ أَنْتَ السَّلَامُ وَمِنْكَ السَّلَامُ، تَبَارَكْتَ ذَا الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ» مسلم.
ከሠውባን(ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው፡- የአላህ መልክተኛ ሶላታቸውን እንዳጠናቀቁ ፡- "አስተግፊሩላህ(አላህ ሆይ ይቅርታህን እጠይቃለሁ) ሶስት ጊዜ ከዛም፡- አላሁምመ አንተ-ሰላም(አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ!) ወሚንከ-ሰላም(ሰላምም የሚገኘው ካንተው ነው)… ይሉ ነበር" (ሙስሊም)፡፡
2. አማኞች ሰላምን እንደሚያገኙ፡- ጌታችን አላህ "አስ-ሰላም" በመሆኑ በሱ ላመኑ ባሪያዎቹ ውስታዊና ውጫዊ ሰላም ያጎናጽፋቸዋል፡፡
" فَأْتِيَاهُ فَقُولَا إِنَّا رَسُولَا رَبِّكَ فَأَرْسِلْ مَعَنَا بَنِي إِسْرَائِيلَ وَلَا تُعَذِّبْهُمْ قَدْ جِئْنَاكَ بِآيَةٍ مِنْ رَبِّكَ وَالسَّلَامُ عَلَى مَنِ اتَّبَعَ الْهُدَى " طه ٤٧
"ወደርሱም ኺዱ፤ በሉትም፡- እኛ የጌታህ መልክተኞች ነን፤ የእስራኤልንም ልጆች፣ ከኛ ጋር ልቀቅ፤ አታሰቃያቸውም፤ ከጌታህ በሆነው ታምር በእርግጥ መጥተንሃልና፤ ሰላምም ቀጥታን በተከተለ ሰው ላይ ይሁን።" (ሱረቱ ጣሀ 47)፡፡
" قُلِ الْحَمْدُ لِلَّهِ وَسَلَامٌ عَلَى عِبَادِهِ الَّذِينَ اصْطَفَى آللَّهُ خَيْرٌ أَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة النمل ٥٩
"(ሙሐመድ ሆይ) በል «ምስጋና ለአላህ ይግባው፡፡ በእነዚያም በመረጣቸው ባሮቹ ላይ ሰላም ይውረድ፡፡ አላህ በላጭ ነውን ወይስ ያ የሚያጋሩት (ጣዖት)፡፡" (ሱረቱ-ነምል 59)፡፡
" وَسَلَامٌ عَلَى الْمُرْسَلِينَ * وَالْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ " سورة الصافات ١٨١-١٨٢ "
"በመልክተኞቹም ላይ ሰላም ይኹን፤ ምስጋናም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይሁን" (ሱረቱ-ሷፍፋት 181-182)፡፡
3. ጀነት ለመግባት ሰበብ መሆኑን፡- ጌታችን አላህ "አስ-ሰላም" በመሆኑ በዚህ ምድር ላይ እኛ አማኝ ባሪያዎቹ ሰላምታን ማብዛት እንዳለብን ተነግሮናል፡፡ ይህንን

የሚያደርግም ጀነት እንደሚገባ ተገልጻል፡፡ ቀጣዩ ሃዲስም ይህን ይገልጻል፡-
عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لَا تَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ حَتَّى تُؤْمِنُوا، وَلَا تُؤْمِنُوا حَتَّى تَحَابُّوا، أَوَلَا أَدُلُّكُمْ عَلَى شَيْءٍ إِذَا فَعَلْتُمُوهُ تَحَابَبْتُمْ؟ أَفْشُوا السَّلَامَ بَيْنَكُمْ» مسلم.
ከአቢ ሁረይራ(ረዲየላሁ ዐንሁ) በተላለፈው ሃዲስ የአላህ መልክተኛ እንዲህ አሉ፡-
"እስካላመናችሁ ድረስ ጀነትን አትገቡም፣ እስካልተዋደዳችሁ ድረስ አታምኑም፣ ከሰራችሁት ሊያዋድዳችሁ የሚችልን ነገር ላመላክታችሁን? ሰላምታን በመሐከላችሁ አብዙ" (ሙስሊም)፡፡

6. "አል-ሙእሚን"

ሀ. ትርጉሙ፡-

"አል-ሙእሚን" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- ለባሪያዎቹ ታማኝ ማለት ነው፡፡ አምላካችን አላህ ለምእመናን ባሪያዎቹ ታማኝና ጸጥታን ሰጪ የሆነ ጌታ ነው፡፡

ለ. አመጣጡ፡-

"አል-ሙእሚን" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፡-
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣
"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" (ሱረቱል ሐሽር 23)፡፡

ሐ. የምንወስደው ትምሕርት፡-

1. እሱን እያመለኩ ምንም ሳያጋሩበት በሱ የታመኑ ባሪያዎቹን በደኅነነቱ ከለላ ውስጥ ይከታቸዋል፡፡ ወደ ቅኑ ጎዳናም ይመራቸዋል፡-
" الَّذِينَ آمَنُوا وَلَمْ يَلْبِسُوا إِيمَانَهُمْ بِظُلْمٍ أُولَئِكَ لَهُمُ الْأَمْنُ وَهُمْ مُهْتَدُونَ " سورة الأنعام ٨٢
"እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ እነዚያ ለእነርሱ ጸጥታ አላቸው፡

፡ እነሱም የተመሩ ናቸው" (ሱረቱል አንዓም 82)፡፡
2. አላህ ለባሪያዎቹ ታማኝ ጌታ በመሆኑ ማንንም የማይበድል መሆኑን፡-
" إِنَّ اللَّهَ لَا يَظْلِمُ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ وَإِنْ تَكُ حَسَنَةً يُضَاعِفْهَا وَيُؤْتِ مِنْ لَدُنْهُ أَجْرًا عَظِيمًا "
سورة النساء ٤٠
"አላህ የብናኝን ክብደት ያህል አይበደልም፤ መልካም ሥራ ብትኾንም ይደራርባታል፤ ከርሱም ዘንድ ታላቅን ምንዳ ይሰጣል።" (ሱረቱ ኒሳእ 40)፡፡
" إِنَّ اللَّهَ لَا يَظْلِمُ النَّاسَ شَيْئًا وَلَكِنَّ النَّاسَ أَنْفُسَهُمْ يَظْلِمُونَ " سورة يونس ٤٤
"አላህ ሰዎችን ምንም አይበድልም፡፡ ግን ሰዎች ነፍሶቻቸውን ይበድላሉ፡፡" (ሱረቱ ዩኑስ 44)፡፡
" وَوُضِعَ الْكِتَابُ فَتَرَى الْمُجْرِمِينَ مُشْفِقِينَ مِمَّا فِيهِ وَيَقُولُونَ يَا وَيْلَتَنَا مَالِ هَذَا الْكِتَابِ لَا يُغَادِرُ صَغِيرَةً وَلَا كَبِيرَةً إِلَّا أَحْصَاهَا وَوَجَدُوا مَا عَمِلُوا حَاضِرًا وَلَا يَظْلِمُ رَبُّكَ أَحَدًا " سورة الكهف ٤٩
"(ለሰው ሁሉ) መጽሐፉም ይቀርባል፤ ወዲያውም ከሐዲዎችን፥ በውስጡ ካለው ነገር ፈሪዎች ሆነው ታያቸዋለህ፤ ዋ ጥፋታችን! ለዚህ መጽሐፍ፥ (ከሥራ) ትንሽንም ትልቅንም የቆጠራት ቢሆን እንጂ የማይተወው ምን አለው? ይላሉም፤ የሠሩትንም ነገር ሁሉ ቀራቢ ሆኖ ያገኙታል፤ ጌታህም አንድንም አይበድልም" (ሱረቱል ከህፍ 49)፡፡
ይቀጥላል

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት
በ አቡ ሃይደር
ክፍል አምስት
በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡
ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሃ 2) ፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56)

ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡
ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡
اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى " سورة طه ٨ "
" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8

7. "አል-ሙሀይሚን"

ሀ. ትርጉም፡-

"አል-ሙሀይሚን" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- የበላይ ተቆጣጣሪ እና ጠባቂ ማለት ነው፡፡ ፈጣሪ አምላካችን አላህ በፍጡራኑ ጉዳይ ፍጹም የበላይ ተቆጣጣሪ ነው፡፡ በንግስናው ስር ከሱ የሚሸሽግ ምንም ነገር የለም፡፡ ዛሬ በምድራችን የአምባገነኖች በደል በዝቶ እውነተኞች ደማቸው ያለ-አግባብ ፈስሶ ብንመለከትና ጌታችንም ያለ ምንም ምድራዊ ቅጣት ዝም ቢላቸው፡ እሱ ለሚያውቀውና ለሚፈልገው ጥበብ ቢፈልገው እንጂ ከግዛቱ መውጣት ችለው አይደለም፡፡ ይሄን እውነታ በቅዱስ ቃሉ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡-
"አላህንም፤ በደለኞች ከሚሠሩት ግፍ ዘንጊ አድርገህ አታስብ፤ የሚያቆያቸው ዓይኖች በርሱ እስከሚፈጡበት ቀን ድረስ ብቻ ነው።" (ሱረቱ ኢብራሂም 42)፡፡
እርሱ ጌታ አላህ ዓለማትን በእውቀቱና በራሕመቱ የከበበ ነው፡፡ ፍጥረታቱን በመላ በችሎታው ስር ያደረገ ነው፡፡ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችላል፡፡ የፈለገውን ነገር "ሁን" ካለው ይሆናል፡፡
"ሰማያትንና ምድርን ያለብጤ ፈጣሪ ነው፤ ነገርንም (ማስገኘት) በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው፡- «ኹን ነው፤» ወዲያውም ይኾናል፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 116)፡፡
"ጌታዬ ሆይ! ሰዉ ያልነካኝ ስሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች፤ ነገሩ እንደዚህሽ ነዉ፤ አላህ የሚሻዉን የፈጥራል፤ አንዳችን በሻ ጊዜ ለርሱ ሁን ይለዋል ወድያዉኑም ይሆናል፥ አላት።" (ሱረቱ አለ-ዒምራን 47)፡፡
"አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ፥ እንደ አዳም ብጤ ነዉ፤ ከዐፈር ፈጠረዉ፤ ከዚያም ለርሱ (ሰዉ) ሁን አለዉ ሆነም" (ሱረቱ አለ-ዒምራን 59)፡፡
"እርሱም ያ ሰማያትንና ምድርን በእውነት የፈጠረ ነው፡፡ «ኹን» የሚልበትንና ወዲያውም የሚኾንበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ቃሉ እውነት ነው…." (ሱረቱል አንዓም 73)፡፡
"ለማንኛውም ነገር (መሆኑን) በሻነው ጊዜ ቃላችን ለርሱ ሁን ማለት ብቻ ነው፤

ወዲያውም ይሆናል።" (ሱረቱ-ነሕል 40)፡፡
"ነገሩም አንዳች ባሻ ጊዜ ሁን ማለት ነው ወዲያው ይሆናልም።" (ሱረቱ ያሲን 82)፡፡
"እርሱ ያ ሕያው የሚያደርግ፣ የሚያሞትም ነው፤ አንዳችን ነገር ባሻም ጊዜየሚለው ሁን ነው፤ ወዲያውም ይሆናል።" (ሱረቱ ጋፊር 68)፡፡
እንዲሁም ይህ "አል-ሙሀይሚን" የሚለው መለኮታዊ ስም ተመልካች የሚልም ትርጉም አለው፡፡ የባሪያዎቹን ንግግርና ስራ ተመልካችና አዋቂ ጌታ በመሆኑ በእውነት ይመሰክራል ይፈርድባቸውማል፡-
"እነዚያ ያመኑ፣ እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ፣ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም፣ መጁሶችም እነዚያም (ጣዖታትን በአላህ) ያጋሩ. አላህ በትንሣኤ ቀን በመካከላቸው በፍርድ ይለያል፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ በእርግጥ ዐዋቂ ነውና።" (ሱረቱል ሓጅ 17)፡፡
ለ. አመጣጡ፡-
"አል-ሙሀይሚን" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርአን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፡-
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣
"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሥ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" (ሱረቱል ሐሽር 23)፡፡
የጌታችን ቃል የሆነው ቅዱስ ቁርአንም ከሱ በፊት የነበሩትን ቀደምት መለኮታዊ መጽሓፍት የሚቆጣጠርና የሚመሰክር በመሆኑ "ሙሀይሚን" የሚል የባሕሪ ስም ተሰጥቶታል፡-
" وَأَنْزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ الْكِتَابِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ... " سورة المائدة ٤٨
"ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን…" (ሱረቱል ማኢዳህ 48)፡፡
8. "አል-ዐዚዝ"
ሀ. ትርጉም፡-
"አል-ዐዚዝ" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉም፡- አሸናፊና የላቀ ማለት ነው፡፡ አላህ በነገሮቹ ሁሉ የበላይ አሸናፊ ነው፡-

"ያም ከምስር የገዛው ሰው ለሚስቱ ፡- መኖሪያውን አክብሪ፤ ሊጠቅመን ወይም ልጅ አድርገን ልንይዘው ይከጀላልና፤ አላት፤ እንደዚሁም ለዩሱፍ (ገዥ ልናደርገውና) የሕልሞችንም ፍች፣ ልናስተምረው በምድር ላይ አስመቸነው፤ አላህም በነገሩ ላይ አሸናፊ ነው፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።" (ሱረቱ ዩሱፍ 21)፡፡

"እነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩት እነዚያ በጣም በወራዶቹ ውስጥ ናቸው።አላህ ፡- እኔ በእርግጥ አሸንፋለሁ፤ መልክተኞቼም (ያሸንፋሉ ሲል)፤ ጽፏል። አላህ ብርቱ አሸናፊ ነውና።" (ሱረቱል ሙጃደላህ 21)፡፡

አሸናፊነት የጌታችን ባህሪ ነው፡፡

" الَّذِينَ يَتَّخِذُونَ الْكَافِرِينَ أَوْلِيَاءَ مِنْ دُونِ الْمُؤْمِنِينَ أَيَبْتَغُونَ عِنْدَهُمُ الْعِزَّةَ فَإِنَّ الْعِزَّةَ لِلَّهِ جَمِيعًا " سورة النساء ١٣٩

"እነዚያ ከምእመናን ሌላ ከሐዲዎችን ወዳጆች አድርገው የሚይዙ፣ እነሱ ዘንድ ልቅናን ይፈልጋሉን? ልቅናም ሁሉ ለአላህ ብቻ ነው።" (ሱረቱ-ኒሳእ 139)፡፡

" وَلَا يَحْزُنْكَ قَوْلُهُمْ إِنَّ الْعِزَّةَ لِلَّهِ جَمِيعًا هُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ " سورة يونس ٦٥

"ንግግራቸውም አያሳዝንህ፡፡ ኀይል ሁሉ በሙሉ የአላህ ብቻ ነውና፡፡ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነው፡፡" (ሱረቱ ዩኑስ 65)፡፡

" مَنْ كَانَ يُرِيدُ الْعِزَّةَ فَلِلَّهِ الْعِزَّةُ جَمِيعًا إِلَيْهِ يَصْعَدُ الْكَلِمُ الطَّيِّبُ وَالْعَمَلُ الصَّالِحُ يَرْفَعُهُ وَالَّذِينَ يَمْكُرُونَ السَّيِّئَاتِ لَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌ وَمَكْرُ أُولَئِكَ هُوَ يَبُورُ " سورة فاطر ١٠

"ማሸነፍን የሚፈልግ የሆነ ሰው፣ አሸናፊነት ለአላህ ብቻ ነው፤ (እርሱን በመግገዛት ይፈልገው)፤ መልካም ንግግር ወደርሱ ይወጣል፤ በጎ ሥራም ከፍ ያደርገዋል፤ እነዚያም መጥፎ ሥራዎችን የሚዶልቱ፣ ለነሱ ብርቱ ቅጣት አላቸው፤ የነዚያም ተንኮል እርሱ ይጠፋል።" (ሱረቱ ፋጢር 10)፡፡

ለ. አመጣጡ፡-

"አል-ዐዚዝ" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ 92 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡

" هُوَ الَّذِي يُصَوِّرُكُمْ فِي الْأَرْحَام كَيْفَ يَشَاءُ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة آل عمران ٦

"እርሱ ያ በማሕፀኖች ዉሰጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነዉ። ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊዉ ጥበበኛዉ ነዉ።" (ሱረቱ አለ-ዒምራን 6)፡፡

" وَالشَّمْسُ تَجْرِي لِمُسْتَقَرٍّ لَهَا ذَلِكَ تَقْدِيرُ الْعَزِيزِ الْعَلِيم " سورة يس ٣٨

"ፀሐይም ለርሷ ወደሆነው መርጊያ ትሮጣለች ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው።" (ሱረቱ ያሲን 38)፡፡

" بِنَصْرِ اللَّهِ يَنْصُرُ مَنْ يَشَاءُ وَهُوَ الْعَزِيزُ الرَّحِيمُ " سورة الروم ٥
"በአላህ እርዳታ (ይደሰታሉ) የሚሻውን ሰው ይረዳል፥ እርሱም አሸናፊው አዛኙ ነው።" (ሱረቱ-ሩም 5)፡፡
ሐ. ከዚህ መለኮታዊ ስም የምንማረው፡-
1. አላህ የእልቅና ባለቤት መሆኑን፡-
" سُبْحَانَ رَبِّكَ رَبِّ الْعِزَّةِ عَمَّا يَصِفُونَ " سورة الصافات ١٨٠
"የማሸነፍ ጌታ የሆነው ጌታህ ከሚሉት ሁሉ ጠራ" (ሱረቱ-ሷፍፋት 180)፡፡
2. አማኝ ባሪያዎቹን እንደሚያልቅ፡-
" يَقُولُونَ لَئِنْ رَجَعْنَا إِلَى الْمَدِينَةِ لَيُخْرِجَنَّ الْأَعَزُّ مِنْهَا الْأَذَلَّ وَلِلَّهِ الْعِزَّةُ وَلِرَسُولِهِ وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَلَكِنَّ الْمُنَافِقِينَ لَا يَعْلَمُونَ " سورة المنافقون ٨
"ወደ መዲና ብንመለስ አሸናፊው ወራዳውን በእርግጥ ከርሷ ያወጣል ይላሉ፤ አሸናፊነትም ለአላህ፣ ለመልክተኛውና፣ ለምእምናን ነው፤ ግን መናፍቆች አያውቁም።" (ሱረቱል ሙናፊቁን 8)፡፡
" قُلِ اللَّهُمَّ مَالِكَ الْمُلْكِ تُؤْتِي الْمُلْكَ مَنْ تَشَاءُ وَتَنْزِعُ الْمُلْكَ مِمَّنْ تَشَاءُ وَتُعِزُّ مَنْ تَشَاءُ وَتُذِلُّ مَنْ تَشَاءُ بِيَدِكَ الْخَيْرُ إِنَّكَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ " سورة آل عمران ٢٦
"(ሙሐመድ ሆይ!) በል- የንግሥና ባለቤት የሆንክ አላህ ሆይ! ለምትሻዉ ሰዉ ንግሥናን ትሰጣለህ፤ ከምትሻዉም ሰዉ ንግስናን ትገፍፋለህ፤ የምትሻዉንም ሰዉ ታልቃለህ፤ የምትሻዉንም ሰዉ ታዋርዳለህ። መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና።" (ሱረቱ አለ-ዒምራን 26)፡፡
3. በዚህ ስም አላህን መለመን እንደሚቻል፡-
" رَبَّنَا وَابْعَثْ فِيهِمْ رَسُولًا مِنْهُمْ يَتْلُو عَلَيْهِمْ آيَاتِكَ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَيُزَكِّيهِمْ إِنَّكَ أَنْتَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة البقرة ١٢٩
"«ጌታችን ሆይ! በውስጣቸውም ከነሱው የኾነን መልክተኛ በነርሱ ላይ አንቀጾችህን የሚያነብላቸውን መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራቸውን (ከክህደት) የሚያጠራቸውንም ላክ፤ አንተ አሸናፊው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና» " (ሱረቱል በቀራህ 129)፡፡
4. ቅዱስ ቁርኣን የአሸናፊው አላህ ቃል በመሆኑ ከፊቱም ሆነ ከኋላው ውሸት ሊቀርበው የማይችል አሸናፊ አድርጎታል፡-
" إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا بِالذِّكْرِ لَمَّا جَاءَهُمْ وَإِنَّهُ لَكِتَابٌ عَزِيزٌ * لَا يَأْتِيهِ الْبَاطِلُ مِنْ بَيْنِ يَدَيْهِ وَلَا مِنْ خَلْفِهِ تَنْزِيلٌ مِنْ حَكِيمٍ حَمِيدٍ " سورة فصلت ٤٢-٤١
"እነዚያ በቁርአን፣ እርሱ አሸናፊ መጽሐፍ ሲሆን፣ በመጣላቸው ጊዜ የካዱት

(ጠፊዎች ናቸው)።ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም፤ ጥበበኛ ምስጉን ከሆነውጌታ የተወረደ ነው።" (ሱረቱ ፉሲለት 41-42)፡፡
9. "አል-ጀባር"
ሀ. ትርጉም፡-
"አል-ጀባር" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- ኃያልና ጠጋኝ ማለት ነው፡፡ ሁሉም ነገር በኃያልነቱ ስር የተንበረከከ በመሆኑ አላህ "አል-ጀባር" ይባላል፡፡ ዳካማዎችን ጉልበት በመለገስ የሚጠግን፣ የተሰበረ ልብን ተስፋ በመሙላት የሚጠግን፣ ድኃን በማብቃቃት የሚጠግን፣ ህመምተኞችን በማዳን የሚጠግን፣ አማኞችን በሚደርሰባቸው ሙሲባ ጽናትን በመለገስ የሚጠግን በመሆኑ አላህ "አል-ጀባር" ይባላል፡፡
ለ. አመጣጡ፡-
"አል-ጀባር" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርአን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፡-
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣
"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" (ሱረቱል ሐሽር 23)፡፡
አላህ ኃያልና የባሮቹን ድክመት ጠጋኝ ጌታ በመሆኑ አንድ ሙስሊም በሩኩእና በሱጁድ ላይ ሲሆን ተከታዩን ዱዓ ያደርጋል፡-
"ሱብሓነ ዚል-ጀበሩቲ ወል-መለኩቲ ወል-ኪብሪያኢ ወል-ዐዘማህ" (አቡ ዳዉድ 873፣ ነሳኢይ 1131፣ አሕመድ 23980)፡፡
(የኃያልነት፣ የግዛት፣ የኩራትና የታላቅነት ባለቤት የሆነው አላህ ከጉድለት ሁሉ ጠራ) ማለት ነው፡፡
እንዲሁም በሁለቱ ሱጁዶች መሓል ሲቀመጥ እንዲህ ይላል፡-
"አላሁምመ ኢግፊር ሊ፣ ወርሐምኒ፣ ወጅቡርኒ፣ ወህዲኒ፣ ወርዙቅኒ" (ቲርሚዚይ)፡፡
(አላህ ሆይ! ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፣ እዘንልኝም፣ ጠግነኝ፣ ቅኑን ጎዳና ምራኝ፣ ሲሳይንም ለግሰኝ) ማለት ነው፡፡
ፍጹም ኃያልነት የጌታ አላህ ብቻ በመሆኑ በምድር ላይ ማንም በማንም ላይ የበላይ መሆንን ከፈለገ አላህ ያዋርደዋል፡፡ የሀቅንም መንገድ እንዳይቀበል ልቡ ይታሸጋል፡

-
" الَّذِينَ يُجَادِلُونَ فِي آيَاتِ اللَّهِ بِغَيْرِ سُلْطَانٍ أَتَاهُمْ كَبُرَ مَقْتًا عِنْدَ اللَّهِ وَعِنْدَ الَّذِينَ آمَنُوا كَذَٰلِكَ يَطْبَعُ اللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ قَلْبِ مُتَكَبِّرٍ جَبَّارٍ " سورة غافر ٣٥

"እነዚያ፤ የመጣላቸው አስረጅ ሳይኖር፣ በአላህ ታምራቶች የሚከራከሩ (ክርክራቸው) አላህ ዘንድና እነዚያም አመኑት ዘንድ መጠላቱ፣ በጣም ተለቀ፤ እንደዚሁ አላህ በኩሩ ጨካኝ (ሰው) ልብ ሁሉ ላይ ያትማል።" (ሱረቱ ጋፊር 35)፡፡

ይቀጥላል

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት

በ አቡ ሃይደር

ክፍል ስድስት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሃ 2) ፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56)

ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡
ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡
" ٨ اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ " سورة طه
" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8

10. "አልሙተከቢር"

ሀ. ትርጉም፡-

"አልሙተከቢር" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- ኩራተኛ፡ የኩራት ባለቤት ማለት ነው፡፡ አላህ የሻውን ሰሪ፡ የፈለገውን አድራጊ፡ ፍጹም የበላይ አሸናፊ፡ ስልጣኑ ያልተገደበ ጌታ በመሆኑ "አልሙተከቢር" ይባላል፡፡ የፈለገውን እንደፈለገው ማድረግ ይችላል፡፡ ማንም ለምን? ብሎ ፈቃዱን መቃወም የሚችል ኃይል የለም፡፡ ኩራት በጌታ አላህ ባህሪ ውስጥ የክብርና የምሉእነት መገለጫ ሲሆን፡ በፍጡር ላይ ግን የበታችነትና የውድቀት ምክንያት ነው፡፡ የጠጣውን ውሃ ከሰዓታት በኋላ ሽንት ሆኖ እንዳይወጣ መቆጣጠር ያልቻለ፤ የበላው ምግብ ከሰዓታት በኋላ ቆሻሻ ሆኖ እንዳይወጣ መቆጣጠር የማይችል አካል እንዴት ሆኖ ይኮራል? እኮ እንዴት? ጌታ አላህ ግን በራሱ የተብቃቃ ኩሩ የሆነ ጌታ ስለሆነ ከስራ እንኳ በኢኽላስ የተሰራውን እንጂ ሪያእ(እዩልን ስሙልኝ) የተቀላቀለበትን አይቀበልም፡-

አቢ ሁረይራህ(ረዲየላሁ ዐንሁ) ባስተላለፈው ሀዲስ ላይ የአላህ መልክተኛ እንዲህ አሉ፡- "አላህ(በሃዲሱል ቁድሲይ ላይ) እንዲህ ይላል፡- እኔ ከተጋሪዎችና ከሚያጋሩብኝም ነገር የተብቃቃሁ ነኝ፡፡ በኔ ላይ ሌላን አካል አጋርቶ አንድን ስራ የሰራ ሰው (በስራው)ማጋራቱንም ሰውየውንም (ወዳጋራብኝ ሰው) እተወዋለሁ" (ሙስሊም)፡፡

ለ. አመጣጡ፡-

"አልሙተከቢር" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የመጣው፡-
" هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ ۚ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ " سورة الحشر ٢٣
"እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ፤ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው፣ ኀያሉ

ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።" (ሱረቱል ሐሽር 23)፡፡
ሐ. የምንወስደው ትምሕርት፡-
1. ጌታችን አላህ "አልሙተከቢር" ስለሆን ኩራት የርሱ መለኮታዊ ባሕሪ መሆኑን እንረዳለን፡-
" وَلَهُ الْكِبْرِيَاءُ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة الجاثية ٣٧
"ኩራትም በሰማያትም በምድርም ለርሱ ብቻ ነው፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።" (ሱረቱል ጃሢያህ 37)፡፡
2. ማንም ሰው ሊኮራ እንደማይገባና ይህንንም የሚፈጽም በዱንያ ውርደት በአኼራ ቅጣት እንደሚገጥመው እንረዳለን፡-
"እነዚያ፤ የመጣላቸው አስረጅ ሳይኖር፣ በአላህ ታምራቶች የሚከራከሩ (ክርክራቸው) አላህ ዘንድና እነዚያም አመኑት ዘንድ መጠላቱ፣ በጣም ተለቀ፤ እንደዚሁ አላህ በኩሩ ጨካኝ (ሰው) ልብ ሁሉ ላይ ያትማል።" (ሱረቱ-ጋፊር 35)፡፡
"በትንሣኤ ቀንም፣ እነዚያን በአላህ ላይ የዋሹትን፣ ፊቶቻቸው የጠቆሩ ሆነው ታያቸዋለህ፤ በገሀነም ውስጥ ለትዕቢተኞች መኖሪያ የለምን?" (ሱረቱ-ዙመር 60)፡፡
"የገሀነምን በርሮች፣ በውስጧ ዘውታሪዎች ስትሆኑ ግቡ (ይባላሉ)፤ የትዕቢተኞችም መኖሪያ (ገሀነም) ምን ትከፋ!" (ሱረቱ ጋፊር 76)፡፡
"እነዚያም የካዱት በእሳት ላይ በሚጋፈጡ ቀም ጣፋጮቻችሁን በአነስተኛይቱ ሕይወታችሁ አሳልፋችሁ በርሷም ተጣቀማችሁ ስለዚህ በምድር ላይ ያለ አግባብ ትኮሩ በነበራችሁትና ታምጡ በነበራችሁት ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትመነዳላችሁ (ይባላል)።" (ሱረቱል አሕቃፍ 20)፡፡
እንድንኮራስ የሚያደርገን ምን አለንና? በመሬት ብንጓዝ የኛን ምልክት እንኳ ላዩዋ ላይ የማናሳርፍ፡ ብንዘል ደግሞ ተራራ የማንደርስ ነን፡-
"በምድርም ላይ የተንበጣረርክ ሆነህ አትኺድ፤ አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና፣ በርዝመትም ፈጽሞ ጋራዎችን አትደርስምና።" (ሱረቱል ኢስራእ 37)፡፡
"ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር፤ በምድርም ላይ ተንጠብርረህ አትኺድ፤ አላህ ተንበጥራሪን፣ ጉረኛን ሁሉ አይወድምና።" (ሱረቱ ሉቅማን 18)፡፡
አምሩ ኢብኑ ሹዐይብ ከአባቱ፡ አባቱ ደግሞ ከአያቱ፡ አያቱ ከነቢያችን(ሰለላሁ

ዐለይሂ ወሰለም) ሰምቶ እንዳስተላለፈልን እንዲህ አሉ፡- "ኩራተኞች የቂያም እለት እንደ ቀይ ጉንዳን አናሳ ሁነው ይቀሰቀሳሉ፡፡ ውርደት ከየ-አቅጣጫው ይከባቸዋል፡ ፡ ቡለስ ወደተባለው ጀሐነም እስር ቤት ይነዳሉ…." (ቲርሚዚይ)፡፡
ዐብደላህ ኢብኑ መስዑድ(ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን ደግሞ የአላህ መልክተኛ እንዲህ አሉ፡- "በልቡ ላይ የጎመን ዘር ፍሬ ያህል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡ አንድ ሰውም መልክተኛውን፡- ሰውው ልብሱና ጫማው ጥሩ እንዲሆንለት ይፈልጋል(ይሄ ኩራት ነውን?) ሲል፡- እሳቸውም፡- አላህ ውብ ጌታ ነው ውበትንም ይወዳል፡፡ ኩራት ግን ሐቅን አለመቀበልና ሰውን በንቀት መመልከት ነው" (ሙስሊም)፡፡
3. አላህንም ስንገዛው በመተናነስና በመዋረድ ስሜት ዝቅ ብለን ከኩራት ርቀን መሆን እንዳለበት እንማራለን፡-
"እነዚያ እጌታህ ዘንድ ያሉት (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፤ ያወድሱታልም፤ ለርሱም ብቻ ይሰግዳሉ።" (ሱረቱል አዕራፍ 206
"ለአላህም በሰማያት ያለው ከተንቀሳቃሻም በምድር ያለው ሁሉ መላክትም ይሰግዳሉ፤ እነርሱም አይኮሩም።" (ሱረቱ-ነሕል 49)፡፡
"በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉም የርሱ ነው፤ እርሱ ዘንድ ያሉትም (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፤ አይሰለቹምም።" (ሱረቱል አንቢያእ 19)፡፡
"ጌታችሁም አለ፡- ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና፤ እነዚያም እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።" (ሱረቱ ጋፊር 60)፡፡
11. "አል-ኻሊቅ"
ሀ. ትርጉም፡-
"አል-ኻሊቅ" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- ፈጣሪ ማለት ነው፡፡ አላህ የዩኒቨርሱ(ፍጥረተ ዓለሙ) የምናየውንም ሆነ የማናየውንም ነገር ሁሉ ብቻውን የፈጠረ ነው፡፡
"(እርሱ) ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው፡፡ ለእርሱ ሚስት የሌለችው ሲኾን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል? ነገርንም ሁሉ ፈጠረ፡፡ እርሱም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡" (ሱረቱል አንዓም 101)፡፡
"(እርሱ) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና የርሱ ብቻ የሆነ ልጅንም ያልያዘ፣ በንግሥናውም ተጋሪ የሌለው፣ ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና፣ በትክክልም ያዘጋጀው ነው።" (ሱረቱል ፉርቃን 2)፡፡
"ይህ ጌታችሁ አላህ ነው፡፡ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም፡፡ ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡

ስለዚህ ተገዙት፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው፡፡" (ሱረቱል አንዓም 102)፡፡
"አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።" (ሱረቱ-ዙመር 62)፡፡
ለ. አመጣጡ፡-
"አል-ኻሊቅ" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ 11 ጊዜ ተጠቅሷል፡-
" هُوَ اللَّهُ الْخَالِقُ الْبَارِئُ الْمُصَوِّرُ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى يُسَبِّحُ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة الحشر ٢٤
"እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው ቅርጽን አሳማሪው ነው፤ ለርሱ መልካሞች ስሞች አሉት፤ በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለርሱ ያሞግሳል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።" (ሱረቱል ሐሽር 24)፡፡
" أَفَرَأَيْتُمْ مَا تُمْنُونَ * أَأَنْتُمْ تَخْلُقُونَهُ أَمْ نَحْنُ الْخَالِقُونَ " سورة الواقعة ٥٨-٥٩
"(በማኅፀኖች) የምታፈሱትን አያችሁትን? እናንተ ትፈጥሩታላችሁን? ወይስ እኛ ፈጣሪዎቹ ነን።" (ሱረቱል ዋቂዓህ 58-59)፡፡
ሐ. የምንወስደው ትምሕርት፡-
1. ከአላህ በስተቀር መፍጠር የሚችል እንደሌለ፡- የሌለ ነገርን መፍጠርና ማስገኘት የአላህ ባሕሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ባሕሪው ምንም ተጋሪ ለውም፡-
" يَا أَيُّهَا النَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَاسْتَمِعُوا لَهُ إِنَّ الَّذِينَ تَدْعُونَ مِنْ دُونِ اللَّهِ لَنْ يَخْلُقُوا ذُبَابًا وَلَوِ اجْتَمَعُوا لَهُ وَإِنْ يَسْلُبْهُمُ الذُّبَابُ شَيْئًا لَا يَسْتَنْقِذُوهُ مِنْهُ ضَعُفَ الطَّالِبُ وَالْمَطْلُوبُ " سورة الحج ٧٣
"እላንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምስሌ ተገለጸላችሁ ለእርሱም አድምጡት፤ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው (ጣዖታት) ዝምብን ፈጽሞ አይፈጥሩም፤ ለርሱ (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳ (አይችሉም) አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከርሱ አያስጥሉትም ፈላጊውም ተፈላጊውም ደከሙ። " (ሱረቱል ሐጅ 73)፡፡
2. የሚፈጥርና የማይፈጥር በምንም መልኩ እንደማይሰተካከሉ፡- አምልኮ የሚገባው መፍጠር የሚችለውን ብቻ እንደኾነ እንማራለን፡-
" أَفَمَنْ يَخْلُقُ كَمَنْ لَا يَخْلُقُ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ " سورة النحل ١٧
"የሚፈጥር፣ እንደማይፈጥር ነውን? አትገሡጹምን ?" (ሱረቱ-ነሕል 17)፡፡
" يَا أَيُّهَا النَّاسُ اعْبُدُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُمْ وَالَّذِينَ مِنْ قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ " سورة البقرة ٢١

"እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 21)፡፡

ይቀጥላል

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት

በ አቡ ሃይደር

ክፍል ሰባት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሃ 2) ፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56)

ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡
ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡
" اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى " سورة طه ٨ "
" አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8
12. "አል-ባሪእ"
ሀ. ትርጉሙ፡-
"አል-ባሪእ" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- ፈጣሪ፣ ከኢምንት አስገኚው ማለት ነው፡፡ በቁጥር 11 ላይ ካየነው "አል-ኻሊቅ" ከሚለው መለኮታዊ ስም ብዙም አይለያይም፡፡ አል-ኢማሙ-ዘመኽሸሪ ደግሞ "አል-ባሪእ" የሚለውን ሲተረጉሙት፡- ፍጥረቱን ከነውር ያጸዳ፣ በስራው እንከን አልባ የሆነ ብለውታል፡፡ ምክንያቱም የዚህ ስም ሐረግ(ስርወ-ግንዱ) "በረአ" የሚል ሲሆን፡ ትርጉሙም ነጻ ወጣ ዳነ የሚል ነው፡፡ ስለዚህ አላህ "አል-ባሪእ" ነው ስንል፡ ስራው ከነውርና ከጉድለት የጠራ ነው ለማለት ነው ይላሉ፡፡ ለዚህ አቋማቸውም ተከታዩን የቁርኣን አንቀጽ ያቀርባሉ፡-
" الَّذِي خَلَقَ سَبْعَ سَمَاوَاتٍ طِبَاقًا مَا تَرَى فِي خَلْقِ الرَّحْمَنِ مِنْ تَفَاوُتٍ فَارْجِعِ الْبَصَرَ هَلْ تَرَى مِنْ فُطُورٍ " سورة الملك ٣
"ያ ሰባትን ሰማያት የተነባበሩ ሆነው የፈጠረ ነው። በአልረሕማን አፈጣጠር ውስጥ ምንም መዛነፍን አታይም። አይንህንም መልስ፤ ከስንጥቆች አንዳችን ታያለህን?" (ሱረቱል ሙልክ 3)፡፡
ከፊል ሊቃውንቶች እንደሚገልጹት፡- "አል-ባሪእ" የሚለው መለኮታዊ ስም በአብዘኃኛው ግልጋሎት ላይ የሚውለው ሕያዋን ፍጥረታትን ለማመልከት ነው፡፡ ግዑዛን ፍጥረታትን ለመግለጽ አይደለም የሚል ነው ወላሁ አዕለም፡፡
ለ. አመጣጡ፡-
"አል-ባሪእ" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ ሶስት ጊዜ ተጠቅሷል፡-

" هُوَ اللَّهُ الْخَالِقُ الْبَارِئُ الْمُصَوِّرُ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى يُسَبِّحُ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة الحشر ٢٤

"እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው ቅርጽን አሳማሪው ነው፤ ለርሱ መልካሞች ስሞች አሉት፤ በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለርሱ ያሞግሳል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።" (ሱረቱል ሐሽር 24)፡፡

" وَإِذْ قَالَ مُوسَى لِقَوْمِهِ يَا قَوْمِ إِنَّكُمْ ظَلَمْتُمْ أَنْفُسَكُمْ بِاتِّخَاذِكُمُ الْعِجْلَ فَتُوبُوا إِلَى بَارِئِكُمْ فَاقْتُلُوا أَنْفُسَكُمْ ذَلِكُمْ خَيْرٌ لَكُمْ عِنْدَ بَارِئِكُمْ فَتَابَ عَلَيْكُمْ إِنَّهُ هُوَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ " سورة البقرة ٥٤

"ሙሳም ለሕዝቦቹ፡- «ሕዝቦቼ ሆይ! እናንተ ወይፈንን (አምላክ አድርጋችሁ) በመያዛችሁ ነፍሶቻችሁን በደላችሁ፡፡ ወደ ፈጣሪያችሁም ተመለሱ፤ ነፍሶቻችሁንም ግደሉ ይሃችሁ በፈጣሪያችሁ ዘንድ ለናንተ በላጭ ነው» ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በእናንተም ላይ ጸጸትን በመቀበል ተመለሰላችሁ፡፡ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 54)፡፡

13. "አል-ሙሰዊር"

ሀ. ትርጉም፡-

"አል-ሙሰዊር" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉሙ፡- ቅርጽን አሳማሪ፣ ሰዓሊ የሚል ነው፡፡ ፈጣሪ አምላካችን አላህ ፍጥረታቱን እሱ ብቻ በሚፈልገው ቅርጽ ያበጀና ያዘጋጀ ነው፡፡ በመልክም ሆነ በቅርጽ፤ በይዘትም ሆነ በአይነት የተለያዩ የሆኑ ስራዎቹን ገልጾዋል፡፡ በዚህ አለም ላይ ፍጹም ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት ነገሮችን ማግኘት አይቻልም፡፡ ይህ የችሎታውን ወሰን-የለሽነት፣ የጥበቡን ጥልቀት፣ የእውቀቱን ስፋት የሚገልጽ ነው፡፡ ከሰው፣ ከእንስሳት፣ ከነፍሳት፣ ከእጽዋት፣ ከበራሪዎች እና ከመላእክት በቅርጽ የማይመሳሰሉ ስንትና ስንት ፍጥረታት አሉት፡፡

ለ. አመጣጡ፡-

"አል-ሙሰዊር" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ አንድ ጊዜ ተጠቅሷል፡-

" هُوَ اللَّهُ الْخَالِقُ الْبَارِئُ الْمُصَوِّرُ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَى يُسَبِّحُ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة الحشر ٢٤

"እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው ቅርጽን አሳማሪው ነው፤ ለርሱ መልካሞች ስሞች አሉት፤ በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለርሱ ያሞግሳል፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።" (ሱረቱል ሐሽር 24)፡፡

ሐ. ከዚህ የምንወስደው ትምሕርት፡-

1. አላህ የፈለገውን ፍጥረት በፈለገው መልኩ መቅረጽ የሚችል ጌታ መሆኑን፡- መፍጠር የአምላካችን መለኮታዊ ባሕሪው መሆኑን ካመንን፡ የፈጠረውን ፍጥረት ደግሞ ምን አይነት ቅርጽ መያዝ እንዳለበት መወሰንም የሱ መብትና ችሎታ ብቻ ነው ማለት ነው፡-

" هُوَ الَّذِي يُصَوِّرُكُمْ فِي الْأَرْحَامِ كَيْفَ يَشَاءُ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ " سورة آل عمران ٦

"እርሱ ያ በማሕፀኖች ዉሰጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነዉ። ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊዉ ጥበበኛዉ ነዉ።" (ሱረቱ አለ-ዒምራን 6)፡፡

" يَا أَيُّهَا الْإِنْسَانُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ الْكَرِيمِ * الَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّاكَ فَعَدَلَكَ * فِي أَيِّ صُورَةٍ مَا شَاءَ رَكَّبَكَ " سورة الإنفطار ٨-٦

"አንተ ሰው ሆይ በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ? በዚያ በፈጠረህ አካለ ሙሉም ባደረገህ፣ ባስተካከለህም። በማንኛውም በሻው ቅርጽ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ)።" (ሱረቱል ኢንፊጣር 6-8)፡፡

በሶላታችን ውስጥ በሱጁድ ስፍራ ላይ ሆነን ከምናደርጋቸው ዚክሮች አንዱ ይህንን የሚገልጽ ነው፡-

عن علي رضي الله عنه قال: أن رسول الله صلى الله عليه وسلم كان إذا سجد قال : " اللهمَّ لَكَ سَجَدْتُ ، وَبِكَ آمَنْتُ ، وَلَكَ أَسْلَمْتُ ، سَجَدَ وَجْهِي للذِي خَلَقَهُ وَصَوَّرَهُ ، وَشَقَّ سَمْعَهُ وَبَصَرَهُ ، تَبَارَكَ الله أَحْسَنُ الخَالِقِينَ " رواه مسلم.

ዐሊይ ኢብኑ-አቢ ጧሊብ(ረዲየላሁ ዐንሁ) ሲናገሩ እንዲህ አሉ፡- "የአላህ መልክተኛ ሱጁድ ሲያደርጉ፡- ‹‹አላህ ሆይ! ላንተ ሰገድኩ፣ ባንተም አመንኩ፣ ላንተም ታዘዝኩ፣ ፊቴም ለዚያ ለፈጠረውና ቅርጽ ላስያዘው፣ መስሚያውንና መመልከቻውን ለከፈተለት ሰገደ" (ሙስሊም)፡፡

2. አላህ በፈለገው ቅርጽ የተሰራው ፍጥረት ደግሞ እጅጉኑ ያማረና የተዋበ

የማያስቀይም መሆኑንም እንማራለን፡-

" اللَّهُ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ قَرَارًا وَالسَّمَاءَ بِنَاءً وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ وَرَزَقَكُمْ مِنَ الطَّيِّبَاتِ ذَلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمْ فَتَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ " سورة الغافر ٦٤

"አላህ ያ ምድርን መርጊያ ሰማይንም ጣሪያ ያደረገላችሁ ነው፤ የቀረጻችሁም ቅርጻችሁንም ያሳመረ፣ ከጣፋጮችም ሲሳዮች የሰጣችሁ ነው፤ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፤ የዓለማትም ጌታ አላህ ላቀ።" (ሱረቱል ጋፊር 64)፡፡

" خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِالْحَقِّ وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ وَإِلَيْهِ الْمَصِيرُ " سورة التغابن ٣

"ሰማያትንና ምድርን በውነት ፈጠረ፤ ቀረፃችሁም ቅርፃችሁንም አሳመረ፤ መመለሻችሁም ወደርሱ ነው።" (ሱረቱ-ተጋቡን 3)፡፡

" ثُمَّ خَلَقْنَا النُّطْفَةَ عَلَقَةً فَخَلَقْنَا الْعَلَقَةَ مُضْغَةً فَخَلَقْنَا الْمُضْغَةَ عِظَامًا فَكَسَوْنَا الْعِظَامَ لَحْمًا ثُمَّ أَنْشَأْنَاهُ خَلْقًا آخَرَ فَتَبَارَكَ اللَّهُ أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ " سورة المؤمنون ١٤

"ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን፡፡ ቁራጯንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው፡፡ ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው፡፡ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ፡፡" (ሱረቱል ሙእሚኑን 14)፡፡

" الَّذِي أَحْسَنَ كُلَّ شَيْءٍ خَلَقَهُ وَبَدَأَ خَلْقَ الْإِنْسَانِ مِنْ طِينٍ " سورة السجدة ٧

"ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው፣ የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው፥ ነው። " (ሱረቱ-ሰጅዳህ 7)፡፡

" لَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنْسَانَ فِي أَحْسَنِ تَقْوِيمٍ " سورة التين ٤

"ሰውን በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው።" (ሱረቱ-ቲን 4)፡፡

3. ለሕያዋን ፍጥረታት ቅርጽን ማሳመር የአላህ ስራ ስለሆነ፡ ለኛ ሕይወት ያለውን(የሰውም ሆነ የእንሰሳት) ምስል መስራት፣ መቅረጽ እንደማይፈቀድልን እንማራለን፡፡ ምክንያቱም በውስጡ ሩህን በመንፋት ሕይወትን መለገስ አንችልምና፡-

عن عبد الله بن مسعود رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: " أشد

الناس عذابا يوم القيامة رجل قتل نبيا ، أو قتله نبي أو رجل يضل الناس بغير علم ، أو مصور يصور التماثيل " رواه الطبراني وحسنه الشيخ الألباني.
ዐብደላህ ኢብኑ-መስዑድ(ረዲየላሁ ዐንሁ) ባስተላለፉት ሐዲሥ የአላህ ነቢይ እንዲህ አሉ፡- "የቂያም ቀን ቅጣቱ እጅግ የሚበረታባቸው ሰዎች፡- ነቢይን የገደለ ወይም ነቢይ እሱን (በክህደቱ)የገደለው፣ ያለ እውቀት ሰዎችን ያጠመመ፣ (ህይወት ያላቸውን ነገሮች) አምሳል የሚቀርጽ ነው" (ጦበራኒ የዘገቡት፣ ሶሒሑል-ጃሚዕ 1000)፡፡
ይቀጥላል

የአላህ ስሞችና ባሕሪያት
በ አቡ ሃይደር
ክፍል ስምንት
በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡
ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሃ 2) ፡፡ የአላህ

ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አህዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሀቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡
ይህ ዓምድ ከጌታችን አላህ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የምንተዋወቅበት ዓምድ ነው፡፡
" اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاءُ الْحُسْنَىٰ " سورة طه ٨
"አላህ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ለርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።" ሱረቱ ጣሃ 8
14-16 "አል-ገፋር"፣"አል-ገፉር"፣"አል-ጋፊር"
ሀ. ትርጉም፡-
"አል-ገፉር" የሚለው መለኮታዊ ስም ትርጉም፡- በጣም መሐሪ ማለት ነው፡፡
"አል-ገፋር" ደግሞ ፡- ትርጉሙ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን እጅግ በጣም መሐሪ የሚለውን የsuperlative degree form የሚገልጽ ነው፡፡ "አል-ጋፊር" የሚለውም ትርጉሙ ከመጀመሪያው አይለይም፡፡
ጌታችን አላህ ለባሪያዎቹ እጅግ በጣም ርኅሩህ፡ በጣም አዛኝ በመሆኑ፡ በኃጢአት ጊዜም መሐሪያቸው እሱ ብቻ ነው፡፡ ይሕ መሐሪነቱ ነው አማኞችን በልባቸው ተስፋን በመሙላት እሱን ለሚያስደስተው መልካም ስራ እንዲሽቀዳደሙ ከሚጠላው ነገር እንዲርቁ የሚያደርጋቸው፡፡ አማኝ የአላህ ባሪያዎች ሁሌም መልካም ተግባርን ጌታችን ይደስትበታል ብለው ሲሰሩ ሁለት ነገርን ከፊት-ለፊታቸው አድርገው ነው፡-

1. በዚህ መልካም ስራቸው ወደ አላህ በመቃረብ ከቸርነት ማዕዱ (ጀነትን) እንዲያቋድሳቸውና
2. በምድራዊ ሕይወታቸው ላጠፉት ጥፋት ምሕረቱን እንዲለግሳቸው በመሻት ነው፡፡

" إِنَّ الَّذِينَ يَتْلُونَ كِتَابَ اللَّهِ وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَأَنْفَقُوا مِمَّا رَزَقْنَاهُمْ سِرًّا وَعَلَانِيَةً يَرْجُونَ تِجَارَةً لَنْ تَبُورَ * لِيُوَفِّيَهُمْ أُجُورَهُمْ وَيَزِيدَهُمْ مِنْ فَضْلِهِ إِنَّهُ غَفُورٌ شَكُورٌ " سورة فاطر ٣٠-٢٩
"እነዚያ የአላህን መጽሐፍ የሚያነቡ፣ ሶላትንም አስተካክለው ያደረሱ,

ከሰጠናቸውም ሲሳይ በሚስጢርም ሆነ በግልጽ የለገሱ፣ በፍጹም የማትከስርን ንግድ ተስፋ ያደርጋሉ። ምንዳዎቻቸውን ሊሞላላቸው፣ ከችሮታቸውም ሊጨምርላቸው፣ (ተስፋ ያደርጋሉ)፤ እርሱ በጣም መሐሪ አመስጋኝ ነውና።" (ሱረቱ ፋጢር 29-30)፡፡

ለ. አመጣጡ፡-

-"አል-ገፉር" የሚለው መለኮታዊ ስም በቅዱስ ቁርአን ውስጥ 91 ጊዜ ተጠቅሷል፡-

" تَكَادُ السَّمَاوَاتُ يَتَفَطَّرْنَ مِنْ فَوْقِهِنَّ وَالْمَلَائِكَةُ يُسَبِّحُونَ بِحَمْدِ رَبِّهِمْ وَيَسْتَغْفِرُونَ لِمَنْ فِي الْأَرْضِ أَلَا إِنَّ اللَّهَ هُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ " سورة الشورى ٥

"(ከአላህ ፍራቻ) ሰማያት ከበላያቸው ሊቀደዱ ይቀርባሉ፤ መላእክትም ጌታቸውን እያመሰገኑ ያወድሳሉ፤ በምድርም ላለው ፍጡር ምሕረትን ይለምናሉ፤ ንቁ አላህ እርሱ መሐሪው አዛኙ ነው።" (ሱረቱ-ሹራ 5)፡፡

" إِنَّ بَطْشَ رَبِّكَ لَشَدِيدٌ * إِنَّهُ هُوَ يُبْدِئُ وَيُعِيدُ * وَهُوَ الْغَفُورُ الْوَدُودُ " سورة البروج ١٢-١٤

"የጌታህ በኀይል መያዝ ብርቱ ነው። እነሆ እርሱ መፍጠርን ይጀምራል፤ ይመልሳልም። እርሱም ምሕረተ ብዙ ወዳድ ነው።" (ሱረቱል ቡሩጅ 12-14)፡፡

-"አል-ገፋር" የሚለው መለኮታዊ ስም ደግሞ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ 5 ጊዜ ተጠቅሷል፡-

" خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِالْحَقِّ يُكَوِّرُ اللَّيْلَ عَلَى النَّهَارِ وَيُكَوِّرُ النَّهَارَ عَلَى اللَّيْلِ وَسَخَّرَ الشَّمْسَ وَالْقَمَرَ كُلٌّ يَجْرِي لِأَجَلٍ مُسَمًّى أَلَا هُوَ الْعَزِيزُ الْغَفَّارُ " سورة الزمر ٥

"ሰማያትንና ምድርን በውነት ፈጠረ፤ ሌሊትንም በቀን ላይ ይጠቀልላል፤ ፀሐይንና ጨረቃንም ገራ፤ ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ፤ ንቁ እርሱ አሸናፊው መሐሪው ነው።" (ሱረቱ-ዙመር 5)፡፡

" رَبُّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا الْعَزِيزُ الْغَفَّارُ " سورة ص ٦٦

«የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታ አሸናፊው መሓሪው ነው፡፡» (ሱረቱ ሷድ 66)፡፡

-"አል-ጋፊር" የሚለው መለኮታዊ ስም ደግሞ በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ 1 ጊዜ ብቻ ተጠቅሷል፡-
" غَافِرِ الذَّنْبِ وَقَابِلِ التَّوْبِ شَدِيدِ الْعِقَابِ ذِي الطَّوْلِ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ إِلَيْهِ الْمَصِيرُ " سورة غافر ٣
"ኀጢአትን መሐሪ፣ ጸጸትንም ተቀባይ፣. ቅጣተ ብርቱ፣ የልግስና ባለቤት ከሆነው (አላህ የወረደ ነው)፤ ከርሱ በቀር አምላክ የለም፤ መመለሻው ወደርሱ ብቻ ነው።" (ሱረቱ ጋፊር 3)፡፡
ሐ. የምንወስደው ትምሕርት፡-
1. እሱ ጌታችን አላህ ፡- "አል-ገፋር" መሐሪ መሆኑን እና በነዚህ ስሞችም የሚጠራ አምላክ መሆኑን እንረዳለን፡-
" نَبِّئْ عِبَادِي أَنِّي أَنَا الْغَفُورُ الرَّحِيمُ * وَأَنَّ عَذَابِي هُوَ الْعَذَابُ الْأَلِيمُ " سورة الحجر ٤٩-٥٠
"ባሮቼን እኔ መሓሪው አዛኙ እኔው ብቻ መኾኔን ንገራቸው፡፡ ቅጣቴም እርሱ አሳማሚ ቅጣት መኾኑን (ንገራቸው)፡፡" (ሱረቱል ሒጅር 49-50)፡፡
" وَإِنِّي لَغَفَّارٌ لِمَنْ تَابَ وَآمَنَ وَعَمِلَ صَالِحًا ثُمَّ اهْتَدَى " سورة طه ٨٢
"እኔም ለተጸጸተ፣ ላመነም መልካምንም ለሰራ፣ ከዚያም ለተመራ ሰው፣ በእርግጥ መሐሪ ነኝ።" (ሱረቱ ጣሀ 82)፡፡
" يَا مُوسَى إِنَّهُ أَنَا اللَّهُ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ * وَأَلْقِ عَصَاكَ فَلَمَّا رَآهَا تَهْتَزُّ كَأَنَّهَا جَانٌّ وَلَّى مُدْبِرًا وَلَمْ يُعَقِّبْ يَا مُوسَى لَا تَخَفْ إِنِّي لَا يَخَافُ لَدَيَّ الْمُرْسَلُونَ * إِلَّا مَنْ ظَلَمَ ثُمَّ بَدَّلَ حُسْنًا بَعْدَ سُوءٍ فَإِنِّي غَفُورٌ رَحِيمٌ " سورة النمل ٩-١١
"ሙሳ ሆይ! እነሆ እኔ አሸናፊው ጥበበኛው አላህ ነኝ። በትርህንም ጣል (ተባለ ጣለም)፤ እርሷ እንደ ትንሽ እባብ በፍጥነት ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ ፊቱን ዞሮ ሸሸ፤ አልተመለሰምም፤ ሙሳ ሆይ! አትፍራ፤ እኔ መልክተኞቹ እኔ ዘንድ አይፈሩምና፤ ግን የበደለ ሰው ከዚያም ከመጥፎ ሥራው በኋላ መልካምን የለወጠ እኔ መሐሪ አዛኝ ነኝ፤" (ሱረቱ-ነምል 9-11)፡፡
2. ከሱ ውጭ የሚምር እንደሌለ:- ጌታችን አላህ ብቻውን "መሐሪ" ነው፡፡ ከርሱ ውጭ ማንም ኃጢአትን ሊምር የሚችል የለም፡፡

" وَالَّذِينَ إِذَا فَعَلُوا فَاحِشَةً أَوْ ظَلَمُوا أَنْفُسَهُمْ ذَكَرُوا اللَّهَ فَاسْتَغْفَرُوا لِذُنُوبِهِمْ وَمَنْ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا اللَّهُ وَلَمْ يُصِرُّوا عَلَى مَا فَعَلُوا وَهُمْ يَعْلَمُونَ " سورة آل عمران ١٣٥
"ለነዚያም መጥፎ ሥራን በሠሩ፥ ወይም ነፍሶቻቸዉን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታዉሱና ለኀጢአቶቻቸዉ ምሕረትን የሚለምኑ ለሆኑት፣ ከአላህም ሌላ ኀጢአቶችን የሚምር አንድም የለ፤ (በስሕተት) በሠሩትም ላይ እነርሱ የሚያዉቁ ሲኾኑ የማይዘወትሩ ለሆኑት (ተደግሳለች)።" (ሱረቱ አለ-ዒምራን 135)፡፡
" وَمَا يَذْكُرُونَ إِلَّا أَنْ يَشَاءَ اللَّهُ هُوَ أَهْلُ التَّقْوَى وَأَهْلُ الْمَغْفِرَةِ " سورة المدثر ٥٦
"አላህ ካልሻ በስተቀር አይገሠጹም፤ እርሱ (አላህ) የመፈራት ባለቤት የምሕረትም ባለቤት ነው።" (ሱረቱል ሙደሢር 56)፡፡
وعند البخاري من حديث أَبِي بَكْرٍ الصديق رضي الله عنه أنه قال للنبي صلى الله عليه وسلم: " عَلِّمْنِي دُعَاءً أَدْعُو بِهِ فِي صَلاَتِي قَالَ: (قُلِ اللهمَّ إِنِّي ظَلَمْتُ نَفْسِي ظُلْمًا كَثِيرًا وَلاَ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلاَّ أَنْتَ ، فَاغْفِرْ لِي مَغْفِرَةً مِنْ عِنْدِكَ ، وَارْحَمْنِي إِنَّكَ أَنْتَ الغَفُورُ الرَّحِيمُ ) "
አቡ-በክር ሲዲቅ(ረዲየላሁ ዐንሁ) የአላህ ነቢይን(ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እንዲህ አላቸው፡- "በሶላቴ ውስጥ ሆኜ አላህን የምለምንበት ዱዓ አስተምሩኝ፡፡
እሳቸውም፡- ‹‹አላህ ሆይ! እኔ ነፍሴን በጣም ብዙ በድያታለሁ፡ ካንተ በስተቀር ወንጀልን የሚምር የለምና፡ ካንተ ዘንድ የሆነ ምሕረትን ለግሰኝ፡ አንተ መሐሪና አዛኝ ነህና እዘንልኝም›› በል አሉት" (ቡኻሪይ)፡፡
3. የትኛውንም ወንጀል የሚምር እንደሆነ፡- የጌታችን ምሕረት ለፍጥረቱ በመላ ነው፡፡ እሱ የማይምረው ኃጢአት የለም፡-
" الَّذِينَ يَجْتَنِبُونَ كَبَائِرَ الْإِثْمِ وَالْفَوَاحِشَ إِلَّا اللَّمَمَ إِنَّ رَبَّكَ وَاسِعُ الْمَغْفِرَةِ هُوَ أَعْلَمُ بِكُمْ إِذْ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الْأَرْضِ وَإِذْ أَنْتُمْ أَجِنَّةٌ فِي بُطُونِ أُمَّهَاتِكُمْ فَلَا تُزَكُّوا أَنْفُسَكُمْ هُوَ أَعْلَمُ بِمَنِ اتَّقَى " سورة النجم ٥٢
" (እነርሱ) እነዚያ የኃጢያትን ታላላቆችና አስጠያፊዎቹን የሚርቁ ናቸው፤ ግን ትናንሾቹ የሚማሩ ናቸው። ጌታህ ምሕረተ ሰፊ ነውና፤ ከምድር በፈጠራችሁ ጊዜ እናንተም በእናቶቻችሁ ሆዶች ውስጥ ሽሎች በሆናችሁ ጊዜ፣ እርሱ በናንተ (ሁነታ) ዐዋቂ ነው። ነፍሶቻችሁንም አታወድሱ እርሱ የሚፈራውን ሰው ዐዋቂ ነው።"

(ሱረቱ-ነጅም 52)፡፡
" قُلْ يَا عِبَادِيَ الَّذِينَ أَسْرَفُوا عَلَى أَنْفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا مِنْ رَحْمَةِ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ جَمِيعًا إِنَّهُ هُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ " سورة الزمر ٥٣
"በላቸው፡- እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፤ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሐሪው አዛኙ ነውና።" (ሱረቱ-ዙመር 53)፡፡
" وَمَنْ يَعْمَلْ سُوءًا أَوْ يَظْلِمْ نَفْسَهُ ثُمَّ يَسْتَغْفِرِ اللَّهَ يَجِدِ اللَّهَ غَفُورًا رَحِيمًا " سورة النساء ١١٠
"መጥፎም የሚሠራ ሰው ወይንም ነፍሱን የሚበድል ከዚያም (ተጸጽቶ) አላህን ምሕረት የሚለምን አላህን መሐሪ አዛኝ ሆኖ ያገኘዋል።" (ሱረቱ-ኒሳእ 110)፡፡
4. ከለመንነው የሚምረን መሆኑን:- ሁላችንም ኃጢአተኞች ነንና ወደ አላህ ብንመለስ እሱ ይምረናል፡-
" قَالَ لَقَدْ ظَلَمَكَ بِسُؤَالِ نَعْجَتِكَ إِلَى نِعَاجِهِ وَإِنَّ كَثِيرًا مِنَ الْخُلَطَاءِ لَيَبْغِي بَعْضُهُمْ عَلَى بَعْضٍ إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَقَلِيلٌ مَا هُمْ وَظَنَّ دَاوُودُ أَنَّمَا فَتَنَّاهُ فَاسْتَغْفَرَ رَبَّهُ وَخَرَّ رَاكِعًا وَأَنَابَ (٢٤) فَغَفَرْنَا لَهُ ذَلِكَ وَإِنَّ لَهُ عِنْدَنَا لَزُلْفَى وَحُسْنَ مَآبٍ " سورة ص ٢٥-٢٤
"...ዳውድም የፈተንነው መኾኑን ዐወቀ፡፡ ጌታውንም ምሕረትን ለመነ፡፡ ሰጋጅ ኾኖ ወደቀም፡፡ በመጸጸት ተመለሰም፡፡ይህን ነገርም ለርሱ ማርነው፡፡ ለእርሱም እኛ ዘንድ መቅረብ (ክብር) መልካም መመለሻም አለው፡፡" (ሱረቱ ሷድ 24-25)፡
፡
" يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا تُوبُوا إِلَى اللَّهِ تَوْبَةً نَصُوحًا عَسَى رَبُّكُمْ أَنْ يُكَفِّرَ عَنْكُمْ سَيِّئَاتِكُمْ وَيُدْخِلَكُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي مِنْ تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ يَوْمَ لَا يُخْزِي اللَّهُ النَّبِيَّ وَالَّذِينَ آمَنُوا مَعَهُ نُورُهُمْ يَسْعَى بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَبِأَيْمَانِهِمْ يَقُولُونَ رَبَّنَا أَتْمِمْ لَنَا نُورَنَا وَاغْفِرْ لَنَا إِنَّكَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ " سورة التحريم ٨
"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ንጹሕ የሆነችን ጸጸት በመጸጸት ወደ አላህ ተመለሱ፤ ጌታችሁ ከናንተ ኀጢአቶቻችሁን ሊሠርይላችሁ፣ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውንም ገነቶች ሊያስገባችሁ ይከጅላልና፤ አላህ ነቢዩን እነዚያንም ከርሱ

ጋር ያመኑትንበማያሳፍርበት ቀን ብርሃናቸው በፊቶቻቸውና በቀኞቻቸው የሚሮጥ ሲሆን ጌታችን ሆ! ብርሀናችንን ሙላልን፤ ለኛ ምሕረትም አድርግልን፤ አንተ ቤገሩ ሁሉ ቻይ ነህና ይላሉ።" (ሱረቱ-ተሕሪም 8)፡፡

5. ከአቅም በላይ በሆነ ነገር አላህ መሐሪ መሆኑን፡- አላህ ያዘዘንን በአግባቡ ከተገበርን፡ የከለከለንንም ከተጠነቀቅን፡ ነገር ግን በረሐብ ምክንያት ሐላል ምግብ አጥተን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር መጥቶ ህይወትን ከሞት አደጋ ለማትረፍ ብለን ሐራም የነበሩ ምግቦችን(የአላህ ስም ያልተወሳባቸው እርዶች፣ ሳይታረዱ የሞቱ…) ብንበላ እርሱ መሐሪ መሆኑን እንረዳለን፡-

" إِنَّمَا حَرَّمَ عَلَيْكُمُ الْمَيْتَةَ وَالدَّمَ وَلَحْمَ الْخِنْزِيرِ وَمَا أُهِلَّ بِهِ لِغَيْرِ اللَّهِ فَمَنِ اضْطُرَّ غَيْرَ بَاغٍ وَلَا عَادٍ فَلَا إِثْمَ عَلَيْهِ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ " سورة البقرة ١٧٣

"በናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን፣ የእሪያ ሥጋንም፣ በእርሱም (ማረድ) ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው፡፡ ሸፍታና ወሰን አላፊ ሳይኾን (ለመብላት) የተገደደ ሰውም በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 173)፡፡

"... فَمَنِ اضْطُرَّ فِي مَخْمَصَةٍ غَيْرَ مُتَجَانِفٍ لِإِثْمٍ فَإِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ " سورة المائدة ٣

"…በረኃብ ወቅት ወደኃጢያት ያዘነበለ ሳይሆን (እርም የሆኑትን ለመብላት) የተገደደ ሰውም (ይብላ) አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።" (ሱረቱል ማኢዳህ 3)::

" إِنَّمَا حَرَّمَ عَلَيْكُمُ الْمَيْتَةَ وَالدَّمَ وَلَحْمَ الْخِنْزِيرِ وَمَا أُهِلَّ لِغَيْرِ اللَّهِ بِهِ فَمَنِ اضْطُرَّ غَيْرَ بَاغٍ وَلَا عَادٍ فَإِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ " سورة النحل ١١٥

"በናንተ ላይ እርም ያደረገው፣ በክትንና ደምን፣ የአሳማንም ሥጋ፣ ያንንም (በመታረድ ጊዜ) በርሱ ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ብቻ ነው፤ አመጠኛም ወሰን አላፊም ሳይሆን (ለመብላት) የተገደደ ሰው (ይፈቀድለታል)፤ አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።" (ሱረቱ-ነሕል 115)፡፡

ይቀጥላል